DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

ኖቬምበር (November) 2013

# የDCPS ዲስትሪክት-አቀፍ፣ የማንጓጠጥ (Bullying) መከላከያ ፖሊሲ

ርዕሰ መምህር

___________________________________

የርዕሰ-መምህር ኢሜል

___________________________________

የርዕሰ-መምህር ወኪል

___________________________________

የርዕሰ-መምህር ወኪል፣ ኢሜል

___________________________________

## ማውጫዎች


| ክፍል/Section | | ገጽ |
|---|---|---|
| I. | መግቢያ/የማጠቃለያ ሃሳብ | 4 |
| II. | የቀደመ-መነሻ (Background)/በሚያስፈልጉ-ነገሮች ላይ ትንታኔ-ማድረግ | 4 |
| III. | ትርጓሜዎች/Definitions | 6 |
| IV. | ማንጓገጥ-እንዳይፈጸም የሚከለከል | 7 |
| V. | ሕትመት/Publication እና የመገኛ-አድራሻ መረጃ/Contact Information | 7 |
| VI. | የስነ-ምግባር ደንብ/Code of Conduct | 8 |
| VII. | መከላከል (Prevention) | 8 |
| VIII. | ጣልቃ-ገብነት | 9 |
| IX. | የሚያስከትሉት ቅጣቶች እና በየእርምጃው-የሚከናወን ባህሪይ ማረሚያ | 9 |
| X. | የሙያ-ማሳደጊያ (Professional Development) እና ስልጠና | 10 |
| XI. | የማንጓጠጥ ክስተቶችን ሪፖርት-ማድረግ | 11 |
| XII. | የማንጓጠጥ ክስተቶች ላይ ምርመራ-ማድረግ | 12 |
| XIII. | ከበቀል-እርምጃ መከላከል | 13 |
| XIV. | መደበኛ-የሆነ - አቤቱታዎች እና ቅሬታዎች/Appeals | 14 |
| አባሪ/Appendix A---የመረጃ-ምንጭ ማገናኛዎች/Resource Links | | 16 |
| አባሪ/Appendix B---የDCPS የማንጓጠጥ ክስተት ሪፖርት ምሳሌ | | 17 |
| አባሪ/Appendix C---የተማሪ የቅሬታ-ሂደት/Grievance Procedure | | 19 |
| አባሪ/Appendix D---የሦስተኛ-ወገን የቅሬታ ሂደት/Grievance Procedure | | 26 |
| አባሪ/Appendix E---የ'Chapter 25' የቅሬታዎች ሂደት | | 31 |

## I. መግቢያ/የማጠቃለያ ሃሳብ

በጁን (June) 22 ቀን 2012 ላይ፤ የኮሎምብያ ዲስትሪክት የከተማው ምክር ቤት (District of Columbia City Council) - ማንጓጠጥ (Bullying)ን ሁሉን-አቀፍ፣ ከተማ-አቀፍ በሆነ ደረጃ ምላሽ-ለመስጠት፣ የ2012 ታዳጊዎች ላይ ማንጓጠጥን (Bullying) የመከላከል ድንጋጌ (Youth Bullying Prevention Act of 2012)ን፤ አጽድቋል። ፖሊሲው፤ ሁሉንም የዲስትሪክት ኤጀንሲዎች፣ እርዳታ-ሰጪዎች እና ለወጣቶች አገልግሎት የሚሰጡ የትምህርት ተቋማት፣ የማንጓጠጥ መከላከል ፖሊሲ (bullying prevention policy)ን እንዲከተሉ ይጠይቃል። ሕጉ፤ ከኮሎምብያ ዲስትሪክት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ፣ ለወጣቶች አገልግሎት የሚሰጠውን - ማንኛውንም አካል ያካትታል። ሕጉ፤ የዲስትሪክት ኤጀንሲዎችን ማንጓጠጥ (Bullying)ን ለመከላከል - የሚያደርጉትን ጥረቶቻቸውን እና የመከላከል ፖሊሲዎቻቸውን በመፍጠር-ረገድ ባላቸው ሚና ላይ የዲስትሪክት ኤጀንሲዎችን ለመርዳት - የ'Mayor's Task Force on Bullying Prevention'ን ፈጥሯል። ይህ ግብረ-ኃይል (Task Force)፤ በማስረጃ ላይ የተመሰረተ ማንጓጠጥን (Bullying) በመከላከል ረገድ፣ ሞዴል ፖሊሲ/model policyን አዘጋጅቷል።

የማንጓጠጥ መከላከል ሕግ፣ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ያለ እያንዳንዱ የወጣቶች አገልግሎት ኤጀንሲ፣ የሕጉድን ዘጠኝ ክፍሎቹ/elementsን የሚያካትት - የማንጓጠጥ መከላከል ፖሊሲን እንዲያዘጋጅ እና እንዲተገብር ይጠይቃል:

- የማንጓጠጥ (bullying) - ሕጋዊ-የሆነ ትርጓሜው፤
- ማንጓጠጥ (bullying)ን የሚከለክል የጽሁፍ-መግለጫ፤
- ፖሊሲው፤ በኤጀንሲው፣ በትምህርት ተቋሙ ወይም በልገሳ-ሰጪ (grantee) - በሚደገፉ ተግባራት ላይ፣ መሳተፍን የሚመለከት መግለጫ፤
- የሚጠበቀው - የስነምግባት ደንብ/code of conduct፤
- ተለይቶ-የታወቀውን የማንጓገጥ (bullying) ክስተትን - ሊያስከትሉ የሚችሉ መዘዞች ዝርዝር፤ ማንጓጠጥ (bullying)ን ሪፖርት ማድረጊያ-ሂደት፤
- በማንጓጠጥ (bullying) ምርመራ-ላይ የተከሰሱ-ሰዎች ስም እና አድራሻን ያካተተ የምርመራ-ሂደት፤
- የይግባኝ ሂደት (An appeal process)፤
- የማንጓጠጥ (bullying) ክስተቶችን ሪፖርት በማድረግ የሚደርሰውን የበቀል-ሂደት የሚከለከያ መግለጫ።

## II. የቀደመ-መነሻ (Background)/በሚያስፈልጉ-ነገሮች ላይ ትንታኔ-ማድረግ (Needs Analysis)

ማንጓጠጥ (Bullying)፤ በእያንዳንዱ ዓመት - በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ታዳጊ ሰዎች ላይ ተጽዕኖ የሚያደርስ፣ ሃገር-አቀፍ ጉዳይ ነው። ተመራማሪዎች፣ ከማንጓጠጥ (Bullying) ጋር ተያይዘው-የሚመጡትን የረጅም-ጊዜ መዘዞችን፣ ድብርትን፣ የአደንዛዥ ዕፅ አለአግባብ-መጠቀምን፣ የጠኝነት ባህሪያቶችን እና ከትምህርት ቤት መቅረትን ጨምሮ፤ ሰፊ-የሆነ ግንዛቤ-እንዲኖር ያሳደጉ-መሆናቸውን፣ በቅርብ-ጊዜ በተደረገው የማንጓጠጥ (Bullying) ብሄራዊ ውይይታችን-ላይ ግንባር ቀደም ሆኗል። በዚህም ምክንያት፣ ትምህርት ቤቶች እና የአካባቢ የመንግስት-መስተዳድሮች - በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚፈጸመውን - ማንጓጠጥ (Bullying) በብቃት-ለመከላከል እና ለመቀነስ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የሚሄድ ጫና እያጋጠማቸው ነው።[1]

በ2010 በወጣው የታዳጊ-ወጣቶች አስጊ-የሆነ ባህሪይ የዳሰሳ-ጥናት/Youth Risk Behavior Survey (YRBS) ላይ-መሠረት አድርጎ፤ ከስድስተኛ ክፍል እስከ አስራ-ሁለተኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች፣ ከ25 በመቶ በላይ የሚሆኑ የመካከለኛ-ደረጃ ተማሪዎች (ከ6-8ኛ ክፍል) በትምህርት ቤት ውስጥ፣ ቢያንስ አንድ-ጊዜ ጥቃት ደርሶባቸዋል። በግምት 15.8 በመቶ/percent - የሚሆኑት፤ ደህንነታቸው ያልተጠበቀ-ሆኖ ስለተሰማቸው፣ በአንድ ወይም ከዚያ-በላይ ቀናት - ወደ ትምህርት ቤት እንደማይሄዱ፣ ሪፖርት አድርገዋል። ሌሎች 13.9 ከመቶ/percent የሆኑት፣ በትምህርት ቤት ውስጥ ድብደባ-እንዳይደርስባቸው ፈርተውን-የነበሩ ናቸው።

---

[1] የአሜሪካ የትምህርት መምሪያ (U.S. Department of Education)፤ *የስቴት የማንጓጠጥ ሕጎች እና*

የ2010 የ'YRBS' ውጤቶች በተጨማሪም፤ 11.1 ከመቶ/percent የሆኑት የከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች (ከ9-12 ክፍሎች-ውስጥ) ያሉት፣ በትምህርት ቤት ውስጥ ድብደባ እንዳይደርስባቸው ፍርሃት-ያደረባቸው መሆኑ ሪፖርት ተደርጓል።

ከጉዳተኝነት-ጋር የሚገኙ ተማሪዎች፤ ጌ (gay)፣ ሌዝቢያን (lesbian)፣ ከሁለት ፆታ ጋር/bisexual የሆኑ ወይም ትራንስጀንደር (transgender) የሆኑ ተማሪዎች፣ እና ቤት-አልባ የሆኑ ተማሪዎ፤ የማንጓጠጥ/bullying፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት - ዒላማ-ለመሆን የበለጠ ተጋላጭ ሊሆኑ ይችላሉ። የዲሲ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ (The DC Human Rights Act) - ለተማሪዎች እና ለማህበረሰብ አባላት በጣም ሰፊ-የሆነ የጥቃት-ትንኮሳ ጥበቃን-ከሚሰጡት ውስጥ አንዱ-ሲሆን፣ ይህም በሚከተለው መሰረት ነው፤ በዘር፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በዜግነት፣ በፆታ፣ በዕድሜ፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በአካላዊ ገጽታ፣ በፆታዊ አመለካከት፣ በፆታ መለያ ወይም አገላለጽ፣ በቤተሰባዊ ሁኔታ፣ በቤተሰብ ኃላፊነቶች፣ በትምህርት ደረጃ፣ በፖለቲካዊ ዝንባሌ፣ በዘር አመጣጥ (genetic) መረጃ፣ በጉዳተኝነት፣ በገቢ ምንጭ፣ በቤተሰብ ትስስር ውስጥ ባለ ወንጀል ሰለባ መሆን፣ ወይም ደግሞ በመኖሪያ ወይም በንግድ ስፍራ፣ አማካኝነት አድልዎ አያደርግም። DCPS፤ በትምህርት ቤት ማህበረሰብ ውስጥ ለችግር-ተጋላጭ ለሆኑ ሰዎች፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ደጋፊ አካባቢዎችን ለመፍጠር - የተወሰኑ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት።

የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (District of Columbia Public Schools (DCPS)፤ ትምህርት ቤቶቻችን ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ውጤታማ የመማሪያ አካባቢዎች መሆናቸውን ለማረጋገጥ - ከማንጓጠጥ/bullying እና ከሌሎች ጎጂ እና የሚረብሹ-ሁኔታዎች ለመጠበቅ ቁርጠኛ-ሆኖ ይሠራል። በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት፤ በመማሪያ-ክፍሎቹ፣ በመተላለፊያ-ቦታዎቹ/hallways፣ ካፊቴሪያዎች፣ የመጫወቻ ስፍራዎች እና ሌሎች የጋራ-መጠቀሚያ ቦታዎቹ

የDCPS - የዲስትሪክት-አቀፍ ግቡ፣ ማንጓጠጥን (Bullying) የመከላከል አካሄድን፣ በዲስትሪክት እና በትምህርት ቤት ደረጃ - ሁሉም ተማሪዎች ደህንነቱ በተጠበቀ፣ ጤናማ እና ደጋፊ-በሆነ አካባቢ ውስጥ መማር እንዲችሉ፤ በማበረታታት እና ስልቶችን በመተግበር የሚሰራ-ነው። ማንጓጠጥ (Bullying)ን ለመከላከል፤ በጣም ንቁ የሆኑት ዘዴዎቹ፣ በአራት ቁልፍ-ቦታዎች ላይ ያተኩራሉ:

- አዎንታዊ ባህሪይን እና የትምህርት ቤት ባህልን ማሳደግ፤
- የሙሉ ትምህርት ቤትን - መከላከል እና ጣልቃገብነት
- በእያንዳንዱ የማንጓጠጥ (bullying) ክስተት ውስጥ - ምርመራ-ማድረግ
- በማንጓጠጥ (bullying) ክስተቶች ውስጥ፣ ለተሳተፉ ግለሰቦች ድጋፍ መስጠት

የምርምር ሰነዶች፤ ዝቅተኛ-ደረጃ ያለው የማንጓጠጥ/bullying ደረጃዎች እና ከፍተኛ-ደረጃ ያለው የአዎንታዊ የትምህርት ቤት የሁኔታ-አቀራረብ/የባህል ደረጃዎች፤ ከከፍተኛ የትምህርት ዕድገት ደረጃዎች ጋር - እንዲሁም-ደግሞ የተማሪ እና ወላጅ በትምህርት ቤት ላይ ባላቸው-እርካታ ጋር - የተቆራኙ ናቸው። የDCPS የማንጓጠጥ (Bully) መከላከል ፖሊሲ፣ ሞዴል የሆነ የፖሊሲ መስፈርቶችን እና ተመራጭ-የሆነ ልምዶችን ያካትታል። ፖሊሲው እና ይህ ሰነድ፣ ከአምስቱ የካፒታል በቁርጠኝነት ቃል-የመግባት ግቦች/ Capital Commitment Goals ውስጥ - ከሁለቱ ጋር በቀጥታ የተጣጣሙ እና የሚደግፉ ናቸው:

- ግብ/Goal፣ 1 ቢያንስ 70% ተማሪዎቻችን፣ በንባብ እና በሂሳብ ብቃት-ያላቸው ይሆናሉ፣ እና በዲስትሪክቱ ውስጥ ያሉ የላቀ-ደረጃ/advanced ተማሪዎችን ቁጥር በእጥፍ እናሳድገዋለን።
- ግብ/Goal 4፣ 90% ተማሪዎች - ትምህርት ቤት እንወዳለን ይላሉ።

## III. ትርጓሜዎች/Definitions

**"ማንጓጠጥ (Bullying)[2]"** ማለት፤ ማንኛውም ጠንካራ-የሆነ፣ የተስፋፋ ወይም ያልተቋረጠ-የእንቅስቃሴ ክንውን ወይም ባህሪይ፤ በአካላዊም ሆነ በኤሌክትሮኒክ ወይም በቃል (verbal) የተደረገ - ሲሆን

A. በተማሪው - በትክክለኛው ወይም ቀድሞ-በታወቀው፤ ዘር፣ ቀለም፣ ኃሳ፣ ሃይማኖት፣ ብሄራዊ ማንነት፣ ፆታ፣ ዕድሜ፣ የትዳር ሁኔታ፣ የግል ገጽታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም አገላለጽ፣ የአዕምሮ ችሎታ፣ የቤተሰብ ሁኔታ፣ የቤተሰብ ኃላፊነት፣ በኮሌጅ/ዩኒቨርስቲ በመግባት/matriculation፣ ፖለቲካዊ ግንኙነት፣ የዘር-ምንጭ መረጃ፣ የአካል ጉዳተኝነት፣ የገቢ ምንጭ፣ የቤተሰብ ውስጥ በሚገኝ የጥቃት-ሰለባ ሁኔታ፣ በማንኛውም የተማሪው ጥፋት ወይም የመኖሪያ ቦታ-ሁኔታ፣ የንግድ ቦታ ወይም ሌላ ቦታ፤ አንድ ሰው ወይም ቡድን ከማንኛውም ሰው ጋር፣ አንድ ወይም ከዚያ-በላይ ከትክክለኛው ወይም ከተገለጹት ባህሪያት ጋር፤ እና

በተገቢው-ሁኔታ፣ መተንበይ ያለበት:

B.
  a. ተማሪውን - በራሱ ወይም በራሷ ሰውነት ወይም ንብረት ላይ፣ አካላዊ-ጉዳት ያመጣል በሚል ተገቢ-የሆነ ፍርሃት - ተማሪውን ማስቀመጥ፤
  b. በተማሪው አካላዊ ወይም አዕምሮአዊ ጤንነት ላይ፣ ጉልህ የሆነ የጉዳት-ውጤት የሚያደርስ ነገር መፍጠር፣
  c. በተማሪው የቀለም-ትምህርት ክንውን ላይ ወይም በትምህርት-ገበታ መገኘት (attendance) ላይ ጉልህ-በሆነ ሁኔታ መስተጓጎልን መፍጠር፣
  d. በተማሪው የመሳተፍ አቅሙ ላይ ወይም ከትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ወይም አገልግሎቶች የሚያገኘውን ጥቅማ-ጥቅሞች ላይ ጉልህ-የሆነ መስተጓጎልን መፍጠር፤ ወይም
  e. የትምህርት ሂደቱን ወይም የትምህርት ቤት መደበኛ አሰራሩን፣ በቁሳዊ/Materially እና ጉልህ-በሆነ ሁኔታ የሚያውክ።

ማንጓጠጥ (Bullying) - በተጨማሪም-የሚከሰተው፣ ተማሪ ወይም የተማሪዎች ቡድን በሌላ ተማሪ ላይ አላግባብ-የሆነ ዘመቻ ሲያደርጉ፣ ወይም ተማሪ ወይም የተማሪዎች ቡድን ስለሌላ ተማሪ አሉባልታዊ-ወሬ ሲያሰራጭ ነው። በአብዛኛዎቹ ሁኔታዎች፤ ማንጓጠጥ (Bullying) እርስ በእርሳቸው ንዴት-ባላቸው ሁለት ተማሪዎች መካከል - የሚከሰትን፣ የእርስ-በርስ ግጭትን አያካትትም። እንደዚህ ዓይነቱ የግጭት-ሁኔታዎች፣ በኮሎምብያ ዲስትሪክት የማዘጋጃ ቤት ደንቦች (District of Columbia Municipal Regulations (DCMR)፣ የ'Title 5---B'፣ 'Chapter 25' (በዚህ ፖሊሲ ውስጥ እንደ - "Chapter 25" ተብሎ-የተጠቀሰው)፣ በዲሲፕሊን ህግ ስር - ለዲሲፕሊን እርምጃ ተገዢ ናቸው። በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ያሉ ሁሉም የማንጓጠጥ (bullying) ማጣቀሻዎች/references፤ የሳይበር ማንጓጠጥ (cyber bullying)ን እንደሚያካትቱ መረዳት አለባቸው።

**የሳይበር ሟንጓጠጥ (Cyber Bullying)** – ቴክኖሎጂን ወይም የኤሌክትሮኒክ ዲቫይሶችን - እንደ ስልኮችን፣ የሞባይል ስልኮች (cell phones)፣ ኮምፒውተሮች፣ እና ኢንተርኔትን በመጠቀም፣ የሚከናወን ማንጓጠጥ (bullying) ነው። ይህም የሚያካትተው፤ ነገር-ግን በዚህ ብቻ ሳይወሰን፤ ኢሜል፣ ወዲያው-የሚደርስ መልዕክቶችን በመላክ፣ የቴክስት (Text) መልዕክቶች፣ እና በኢንተርኔት ላይ የተለጠፉ-ነገሮች (postings)ን ያካትታል።

**የኤሌክትሮኒክ ግንኙነት-ማድረግ/Electronic communication** – የኢንተርኔት አጠቃቀም እና የሞባይል ቴክኖሎጂ እንደ ድህረ-ገጾች ያሉት፣ የውይይት-ማድረጊያ ቡድኖች - እንደ ወዲያው የሚደርስ መልእክት፣ 'SMS' ቴክስት/text፣ ኢንስተግራም/Instagram ወይም ፌስቡክ/Facebookን - ሌላ ሰውን ለማስፈራራት፣ ለማዋከብ ወይም ለመጉዳት በማሰብ- ጥቅም-ላይ ማዋል።

[2] በታዳጊ-ወጣት ማንጓጠጥ መከላከል ፖሊሲ ድንጋጌ/Youth Bullying Prevention Policy Act 2012 ላይ - ከተሰጠው ትርጉም የተወሰደ

**የርዕሰ-መምህር ወኪል/Principal Designee---** ምርመራዎች/investigationsን የሚያካሂድ እና በርዕሰ-መምህሩ ቦታ-ሆኖ - ግንኙነቶችን የሚሰጥ፤ በርዕሰ-መምህሩ የተወሰነ - ለግንኙነት-የተሰየመ ሰው። እያንዳንዱ ትምህርት ቤት፣ ለግንኙነት-ማድረግ የተወሰውን ሰው - ስም እና የሚገኙበትን የአድራሻ-መረጃ፣ ለወላጆች እና ተማሪዎች ማቅረብ አለበት።
የርዕሰ-መምህሩን ተወካይ - ስም እና አድራሻ፣ በዋናው-ቢሮ (main office) ውስጥ መለጠፍ እና፣ በዚህ ፖሊሲ ሰነድ - ፊት-ለፊት ላይ ባለው-ቦታ ላይ - ይህንን መረጃ ማካተት - የሚመከር-ነው።

**ደህንነቱ-የተጠበቀ ሰው/Safe person** -- ያልመቻቸ-ስሜትን፣ ተቀባይነት-የሌለው ወይም ደህንነት-የሌለው ስሜት የሚፈጥር ፍርሃት ሳይኖረው፤ በተማሪው እና በአንድ-ሰው የሚታመን-መሆኑ የተወሰነ - ምቾት የሚሰጥ ሰው።

**ደህንነቱ-የተጠበቀ ቦታ/Safe space** --- ያልመቻቸ-ስሜትን፣ ተቀባይነት-የሌለው ወይም ደህንነት-የሌለው ስሜት የሚፈጥር ፍርሃት ሳይኖረው፤ ማንም ሰው ለመዝናናት-የሚችልበት እና ሙሉ-ለሙሉ እራሱን ገልጽ-የሚችልበት ቦታ።

**ሠራተኞች/Staff** – አስተማሪዎችን፣ አስተዳዳሪዎችን፣ ካውንስለሮችን፣ የትምህርት ቤት ነርሶችን፣ የካፌቴሪያ ሠራተኞችን፣ የእርዳታ-አገልግሎት ሰጪዎችን፣ የአውቶቡስ ሹፌሮችን፣ አሰልጣኞችን፣ የአትሌቲክስ ዳይሬክተሮችን፣ ድጋፍ-ሰጪ ሠራተኞችን ወይም ባለሙያተኛተኞች (paraprofessionals)ን፣ ነገር-ግን በዚህ ብቻ ያልተወሰነን - ያካትታል።

## IV. ማንጓገጥ-እንዳይፈጸም የሚከለክል

DCPS፤ ሁሉም-ሰው በአክብሮት የሚስተናገድበት እና ማንም በአካልም ሆነ በስሜታዊነት የማይጎዳበትን የትምህርት ቤት አካባቢ በመጠበቅ፣ ለተማሪዎች ጥሩ የመማር ሁኔታዎችን ለማቅረብ ይጥራል። በተማሪዎች የሚደረጉ የማንጓጠጥ (bullying) ድርጊቶች፣ የተከለከሉ ናቸው:

a. በትምህርት ቤት ቅጥር-ግቢዎች ውስጥ፤
b. በማንኛውም በትምህርት ቤት --ስፖንሰር-በተደረገ እንቅስቃሴ ወይም ዝግጅት ላይ፣ እና ከDCPS ጊቢዎች ውጪ:
c. በሕዝብ ወይም የትምህርት ቤት መጓጓዣ - የማቆሚያ-ቦታዎችን ጨምሮ፤
d. የትምህርት ቤት ንብረትን ወይም መሳሪያዎች/equipmentን በመጠቀም፤
e. ወደ ትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት በእግር-በሚሄዱ ጊዜ፤

## V. ሕትመት/Publication እና የመገኛ-አድራሻ መረጃ/Contact Information

ማንጓጠጥን (Bullying) በመከላከል ላይ፣ አጠቃላይ--ትምህርት ቤትን ለመደገፍ፤ ትምህርት ቤቶች - የማንጓጠጥን (Bullying) መከላከል እና ጣልቃገብነት ፖሊሲዎችን እና መመሪያዎችን - ለአስተማሪዎች እና ለሌሎች የትምህርት ቤት ሠራተኞች፣ ተማሪዎች፣ ወላጆች፣ የወላጅ--አስተማሪ ድርጅቶች፣ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች፣ እና ሌሎች ተዛማጅ-የሆኑ ቡድኖችን - በንቃት ማሳወቅ አለባቸው።
በትምህርት ቤቱ--ዙሪያ የተለጠፉትን፣ ፖስተሮች፣ በራሪ-ወረቀቶች፣ 'Connect ED'፣ እና ሁሉንም ሌሎች ከትምህርት ቤት ወደ መኖሪያ-ቤት ግንኙነት-የሚደረግባቸው መንገዶች - ፖሊሲውን እና አዎንታዊ-የሆነ የትምህርት ቤት ሁኔታን ለመገንባት ሆን-ተብሎ ትኩረት የተደረገባቸውን ነገሮች - ግንኙነት-በማድረግ ለማሳወቅ ጥቅም-ላይ ይውላሉ።

የDCPS የማንጓጠጥ ፖሊሲ እና ሁሉም ሪፖርት-የማድረጊያ ሂደቶች ላይ ያሉ መመሪያዎች፤ በDCPS ድህረ-ገጽ ላይ እንዲገኙ-ይደረጋል። ፖሊሲው እና ሁሉም ተዛማጅ-የሆኑ ቅጾች፤ በዲስትሪክቱ ውስጥ የሚገለገሉት ማህበረሰቦች - በሚጠቀሙባቸው ቋንቋዎች ይተረጎማሉ።

የታዳጊ-ወጣት ተሣትፎ ቢሮ (The Office of Youth Engagement(OYE)፤ ከትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራኖች ጋር በመተባበር እና በመቀናጀት፣ የDCPS ማንጓጠጥን የመከላከል ጥረቶችን - የማስተባበር-ኃላፊነት አለበት። ስለ ማንጓጠጥ (bullying) ፖሊሲ እና የDCPS የመከላከያ ጥረቶች ላይ ለሚቀርቡ፣ ሁሉም ጥያቄዎች፣ አስተያየቶች እና ስጋቶች፤ ለህንፃው ርዕሰ-መምህር ወይም ለርዕሰ-መምህሩ ተወካይ ወይም በ'OYE' ውስጥ - ለDCPS እና የትምህርት ቤት ባህል ዳይሬክተር - ተልከው-መቅረብ አለባቸው።

## VI. የስነ-ምግባር ደንብ/Code of Conduct

አዎንታዊ-የሆነ የትምህርት ቤት ባህልን/ሁኔታን መፍጠር እና ጠብቆ-ማቆየት፤ የማንኛውም የማንጓጠጥ መከላከል ፕሮግራም/bullying prevention program፣ ዋናው-መሠረት ነው። የትምህርት ቤት ባህልን ለመገንባት በጣም-ስኬታማው ልምምድ፤ ሙሉ-በሆነው የትምህርት ቤት አቀራረብ ውስጥ፣ ትምህርትን እና የማህበረሰብ አጋሮችን የሚያሳትፍ-መሆኑ ነው። ስልታዊ-የሆነ እና ስልታዊ ለውጥን ለማምጣት፣ የትብብር እና የተቀናጀ ጥረት ያስፈልጋል። የሚከተሉት ባህሪያቶች - አዎንታዊ የትምህርት ቤት ሁኔታዎችን - ይፈጥራል ብሎ DCPS ያምናል:

- ተማሪዎች፣ የሠራተኛ አባላቶች፣ እና ወላጆች - የደህንነት-ጥበቃ ያላቸው፣ የተካተቱ-የመሆን ስሜት እና የተቀባይነት-ስሜት የሚሰማቸው-መሆን፤
- ሁሉም የትምህርት ቤት ማህበረሰብ - በእርስ-በርስ ግንኙነቶቻቸው ውስጥ - አክብሮት፣ ፍትሃዊነት፣ እና ደግነት ያላቸው መሆን፤
- ከአድልዎ እና ከትንኮሳ - ነፃ-የሆኑ፣ ጤናማ-የሆኑ ግንኙነቶችን መገንባት፤
- የመማሪያ አካባቢ እና ስርዓተ-ትምህርቱ፤ የባህሪይ ትምህርትን እና ለስብጥርነት-ያለውን አድናቆት የሚያንጸባርቅ-መሆን፤
- ማንጓጠጥን (Bullying) መከላከል እና ግንዛቤ-መኖር--ለተማሪዎች፣ ሠራተኞች፣ እና ቤተሰቦች ስልቶቹን ማስጨበጫዎችን፤ እንዲማሩ እና እንዲያጠናክሩ-ማድረግ፤ እና
- ተማሪዎች፤ ትርጉም-በሚሰጥ ሁኔታ የተሳተፉ እና ከፍተኛ-በሆነ ሁኔታ በሚጠበቁባቸው አካባቢ ውስጥ፣ ስኬታማ እንዲሆኑ ድጋፍ መስጠት።

DCPS፤ ለተማሪዎች የተቀበሏቸው-መሆኑን፣ ደህንነታቸው የተጠበቀ፣ የተከበሩ እንደሆኑ እንዲሰማቸው እና በዚህም-ሁኔታ፣ ሙሉ-በሙሉ በአካዳሚክ ትምህርታቸው ውስጥ መሳተፍ እንዲችሉ በሚያደርጋቸው-ቦታ ላይ፣ አዎንታዊ የሆነ የትምህርት ቤት ባህልን - ለመፍጠር፣ የሚሰራ-መሆን አለበት።

የDCPS ፖሊሲ፤ የማንጓጠጥ መከላከልን፣ እንደ ሙሉ-የሆነ - ትምህርት ቤት (whole-school) የመከላከል/የጣልቃ-ገብነት አሰራርን የሚያካትቱ ካልሆኑ-በስተቀረ፣ እንደ መከላከል እና ጣልቃገብነት ዘዴዎች - ውጤታማ-ሊሆን እንደማይችል፣ ይገነዘባል። ሙሉ-የሆነ - ትምህርት ቤት አሰራር፤ የሚከተሉትን አካላት/elementsን ያካትታል: መከላከል፣ ጣልቃ-ገብነት፣ የሚያስከትሉትን-መዘዞች፣ ለተደጋገሙ የዲሲፕሊን-ጥሰቶች ቅጣት-መስጠት፣ እና ትኩረት-የተደረገበት የሙያ-ማሳደጊያ (professional development) እና ስልጠና።

## VII. መከላከል (Prevention)

ትምህርት ቤቶች፤ የማንጓጠጥ መከላከል ግንዛቤን ለማሳደግ እንዲችሉ፣ በዓመታዊው የሙያ-ማሳደጊያ/Professional Development እና ስልጠና ውስጥ መካፈል-ይጠበቅባቸዋል። ትምህርት-ቤት አቀፍ-የሆነ በምስክርነት-ላይ መሠረት ያደረገ የማንጓጠጥ መከላከያ ፕሮግራሞች፤ እንደ የአዎንታዊ ባህሪያዊ ድጋፍ-መስጫ ስርዓት አንዱ-አካል ሆኖ እና በሁሉም የክፍል-ደረጃዎች ውስጥ የትምህርት ቤት የማሻሻያ-ጥረቶች ሆኖ - ተፈጻሚ-ይሆናል። የማንጓጠጥ መከላከያ ዘመቻዎች፣ ስብሰባዎች፣ ፕሮግራሞች፣ ሰልፎች፣ ወርሃዊ አከባበሮች፣ ወዘተ… በዓመቱ-ሙሉ ባለው-ጊዜ ውስጥ መቀረጽ እና መፈጸም-አለባቸው።

ስኬታማ-የሆነ የማንጓጠጥ መከላከል ልምዶችን ማስፋፋት እና ባህሪያቶች-መኖር፤ የውሳኔ አሰጣጥ እና የትምህርት ቤት መሻሻል ጥረቶች ላይ በደንብ-የታወቀ ውሳኔን-ለማድረግ ይጠቅማሉ። ከዳሰሳ-ጥናቶች የተገኘው፣ ወጥነት-ያለው እና ተደጋጋሚ-የሆነ የትምህርት ቤት የባህል አመላካቾች ላይ ቁጥጥር-ማድረግ፤ በትምህርት ቤት-አቀፍ ፕሮግራሞች እና በዓላት ላይ የሚሳተፉ ተማሪዎችን - ብዛት፣ ሪፖርት ካርዶች እና የተማሪ ባህሪ የመረጃ-ስብስብ ስርዓቶች (data systems) - አዎንታዊ የትምህርት ቤት ባህል ሲፈጥሩ እና ሲያስተዋውቁ፣ ከግምት ውስጥ ሊገቡ-የሚችሉ ጠቃሚ የመረጃ ምንጮች ናቸው። ይህ መረጃ፤ የባህሪዎችን እና አሳሳቢ አካባቢዎችን ለመለየት ይረዳል፣ እና በደንብ የተገነዘቡትን የውሳኔ-አሰጣጥን - በመከላከል ስልቶች ላይ ለማድረግ የሚያስችል-ሲሆን፣ ነገር-ግን በዚህ ብቻ ሳይወሰን፣ የአዋቂዎች ክትትል፣ሙያዊ እድገት፣ በዕድሜ-ተመጣጣኝነት ያላቸው ስልቶች እና የትምህርት ቤት ድጋፍ አገልግሎቶችን ለመለየት-ይረዳል። የመረጃ-ስብስቡ (data) - የትምህርት ቤትን ጉዳይ ወይም ስጋት ካሳየ፣ በአዎንታዊ የትምህርት ቤት ባህል እና የማንጓጠጥ መከላከል ግንዛቤ (bullying prevention awareness) ዙሪያ-ባለው፣ የቤተሰብ እና የማህበረሰብ ተሳትፎ ስትራቴጂዎች ክፍል/section ውስጥ ባለው፣ በ'Comprehensive School Plan (CSP)' ውስጥ መካተት አለባቸው።

## VIII. ጣልቃ-ገብነት

ለማንጓጠጥን (Bullying) መከላከል፤ ትምህርት ቤቶች ቀጣይነት ያለው ስልጠና እና የሙያ-ማሳደጊያ/professional development - እንዲሰጡ ይጠበቅባቸዋል። ስልጠናው፤ ማንጓጠጥን (bullying) ለመከላከል ንቁ እና አወንታዊ ስልቶችን-ያካተተ፣ እንዲሁም የሚያንጓጥጡ፣ ማንጓጠጥ-የደረሰባቸውን እና ማንጓጠጡን-ሪፖርት ያደረጉ ተመልካች-የነበሩ ተማሪዎች - በአግባቡ ምላሽ ለመስጠት የአሰራር መመሪያዎችን እና ልምዶችን ማካተት አለበት።

ጣልቃ-ገብነቶች፣

- የማንጓጠጥ ባህሪያቶችን ለሚያሳዩ ተማሪዎች፣ ባህሪያቶቹን በሌላ-የመተካት እና በቀላሉ-ስሜታቸን ከሚነካ ሁኔታ-ማስወጫ - ስልጠና-መስጠት:
- ማንጓጠጥን ለመከላከል የታለመው - ቀጣይነት-ያለው ጣልቃገብነት፤ አንጓጣጭ-የሆነውን ተማሪ - ማህበራዊ-ስሜታዊ፣ ባህሪይ እና አካዳሚያዊ ፍላጎቶች ላይ ምላሽ-በመስጠት፤
- የጣልቃገብነት እርምጃዎች ቢወሰዱም-እንኳ - አሁንም-በተደጋጋሚ የሚያንጓጥጡ ተማሪዎች፣ እና እንደ ጥቃት-አድራሾች፣ ተጠቂዎች ወይም ምስክሮች-ሆነው ለተሳተፉ ተማሪዎች፣ የማህበረሰብ እና የአዕምሮ ጤና የመረጃ-ምንጮችን ለይቶ-ማቅረብ፤
- በቀል እና ተጨማሪ-የሆነ የማንጓጠጥ ክስተቶች እንዳይደርሱ ጥበቃ-ከማድረግ ጋር፣ ለተጠቂው የምክር-አገልግሎቶን በመስጠት ድጋፍ-መስጠት፤
- በትምህርት ቤቱ ውስጥ "ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ/safe space" እና "ደህንነታቸው የተጠበቀ ሰዎች/safe people" የመረጃ-ምንጮችን - ማዳበር፤
- በተማሪ የእርዳታ ቡድን (Student Support Team (SST) ሂደት-ውስጥ፣ ለማንጓጣጩ እና ለተጠቂው፣ የተጠናከረ የጣልቃ-ገብነት ዕቅዶችን መቅረጽ።

## IX. የሚያስከትሉት ቅጣቶች እና በየእርምጃው-የሚከናወን ባህሪይ-ማረሚያ

ተማሪዎች፣ ተገቡ-ለሆነ የትምህርት ቤት ባህሪይ እና ቦታዎች - የሚጠበቁባቸውን-ነገሮች እና ደንቦችን እንዲማሩ ለመርዳት፣ ተገቢ-ያልሆነ ባህሪይን በመከላከል ላይ -ማስተማርን፣ መከላከልን እና ጣልቃ-ገብነት ላይ ከፍተኛ-ትኩረት በመስጠት፣ DCPS፤ ቁርጠኛ-ሆኖ ይሠራል። ሊያስከትሉ-የሚችሉት ቅጣቶች፤ ሊለወጡ-የሚችሉ ባህሪያቶችን በመቀየር፣ በመቆጣጠር እና በማስተማር ላይ ትኩረት-በመስጠት፣ ዝቅተኛ-የሆነ አስከፊ-የሆነ ምላሽን ማካታት-አለበት። የማንጓጠጥ፣ የትንኮሳ ወይም የማስፈራራት ድርጊቶችን ለፈጸሙ ተማሪዎች እና፣ በበቀል ወይም በበቀል-ስሜት ለተሰማሩ ተማሪዎች፣ እና የውሸት ክስ የፈጸሙ ተማሪዎች፤ ሊያስከትል-የሚችሉት ቅጣቶች - እንደዚህ ዓይነት ጥፋት መፈጸሙ-ከተረጋገጠ በኋላ፣ ተገቢ-የሆነው ምርመራ ያለማቋረጥ እና ተገቢ-በሆነ መንገድ መተግበር አለባቸው።

በፖሊሲ ውስጥ - በአሁኑ ጊዜ፤ ማንጓጠጥ (Bullying) በ'Chapter 25' መሠረት፣ የ'Tier 3' ጥሰት/infraction የሆነ እና በርካታ-የሆኑ የሚያስከትለውን-ቅጣቶችን ሊያደርስ ይችላል። ትምህርት ቤቶች፤ ከDCPS ፖሊሲዎችና ሂደቶች ጋር የሚጣጣሙ ውጤቶችን እና እያደገ-የሚሄደውን የዲሲፕሊን እርምጃዎችን እንዲወስኑ እና እንዲተገብሩ ይበረታታሉ። የሚከተሉት - ሊያስከትሉ-የሚችሉት ቅጣቶች ዝርዝር ፤ እንደ መምሪያ-ሆነው ተዘርዝረዋል:

- የቃል ዳግም-ትዕዛዝ መስጫ/ተግሳጽ
- የአስተማሪ/የተማሪ ኮንፈረንስን
- የአስተዳዳሪ/የተማሪ ኮንፈረንስ
- ወላጅን ማነጋገር (በጽሁፍ ወይም በስልክ)
- የወላጅ ኮንፈረንስ
- በጊዜያዊነት ተማሪን ከመማሪያክፍል ማስወገድ
- የባህሪይ ኮንትራክት/Behavior contract
- በትምህርት ቤት ውስጥ የዲስፕሊን እርምጃ
- በትምህርት ቤት ውስጥ እገዳ/suspension
- ከትምህርት-ቤት ውጪ እገዳ (Out of school suspension)

የትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪዎች - የሚያስከትሉትን ቅጣቶች የመተግበር ውሳኔ የሚኖራቸው-ቢሆንም እንኳን፣ የሚያስከትለው-ቅጣት ዓላማ - የሚከተለው መሆን አለበት፡

- በተገቢው-ሁኔታ የማንጓጠጥ ባህሪውን ለማረም፣
- ሌላ የማንጓጠጥ ሁኔታ ወይም በቀል እንዳይፈጠር መከላከል፣
- የማንጓጠጡ ዒላማ-የሆነውን ሰው-ላይ ጥበቃ-ማድረግ፣ እና
- ይህ በመተግበር-ላይ፤ ለእያንዳዱ ክስተት ልዩ-ሊሆን በሚችል ሁኔታ እና በክስተቱ-ሁኔታ ላይ ተመርኩዞ ክብደቡን እና ዘዴው የተለያየ-መሆንን፣ ማንጓጠጡን የሚያደርገው ሰው የዕድገታዊ-ሁኔታ ዕድሜ እና ማንጓጠጡን ከሚያደርገው-ሰው ማንኛውም የባህሪይ ችግር ታሪክ-ከዚህ በፊት መኖሩ-ላይ፣ ተለዋዋጭነት-ማሳየት።

## X. የሙያ-ማሳደጊያ (Professional Development) እና ስልጠና

ርዕሰ-መምህራን፤ አስተማሪዎችን እና የትምህርት ቤቱን ሠራተኞች ስለ ማንጓጠጥ መከላከል እና አዎንታዊ-የሆነ የትምህርት ቤት ሁኔታን ለማበረታታት፣ ስልቶችን ለማስተማር - ዓመታዊ የሙያ-ማሳደጊያ/professional development ፕሮግራሞችን፣ መፍጠር እና መስጠት ይጠበቅባቸዋል። 'OYE'፤ ለትምህርት ቤት-ተኮር የሙያ-ማሳደጊያ የመረጃ-ምንጭ ሆኖ ያገለግላል እና ከማዕከላዊ ቢሮ ክፍሎች ጋር በመሆን፣ በትምህርት ቤት-ውስጥ ላልሆኑ ሠራተኞች፤ እንደ አሰልጣኞች፣ የአውቶቡስ ሾፌሮች እና የ'resource officers'ን፣ ስልጠና ለመስጠት ይሰራል።

DCPS፤ ከስልጠና በተጨማሪ የማንጓጠጥ ጥቃቶችን ለመከላከል፣ ለመለየት እና ምላሽ-ለመስጠት የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችን እና እውቀትን ለመገንባት፤ ሠራተኞች ቀጣይነት-ያለው የሙያ-ማሳደጊያ/professional development እንደሚያስፈልጋቸው ይገነዘባል። 'OYE' የመረጃ-ምንጮችን፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን እና ተገቢ-የሆኑ የስልጠና ዕድሎችን ሲያገኝ፣ ይፋ-ያደርጋል።

# XI. የማንጓጠጥ ክስተቶችን - ሪፖርት-ማድረግ

ማንጓጠጥ ወይም አሉ-ተብሎ የተጠረጠረው ማንጓጠጥ - በአካልም ሆነ በጽሁፍ (ስምን-የማይጠቅሰውን ጨምሮ) ለትምህርት ቤት ሠራተኞች፣ ሪፖርት-መደረግ የሚችል ነው። DCPS - ሁሉም የሠራተኛ አባላት እና የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች ያዩትን የማንጓጠጥ ወይም የበቀል ክስተቶች - ሪፖርት እንዲያደርጉ ወይም ለርዕሰ-መምህሩ ወይም ለርዕሰ-መምህሩ ተወካይ - እንዲያውቁ ይጠብቃል።
ለተጨማሪ መረጃ፣ ከታች-የሚገኘውን፣ ‘Section XIV’ን ተመልከቱ።

ማንጓጠጥ-የደረሰባቸው ወይም የጥቃት ድርጊቶችን የሚያውቁ ተማሪዎች፤ ይህንን ባህሪይ - ለርዕሰ-መምህሩ ወይም ለርዕሰ-መምህሩ ተወካይ - ሪፖርት እንዲያደርጉ መበረታታት አለባቸው።

ስለክስተቶቹ የሚያውቁ ውላጆች ወይም ሌላ አዋቂዎች፤ ይህንን ባህሪይ - ለርዕሰ-መምህሩ ወይም ለርዕሰ-መምህሩ ተወካይ - ሪፖርት እንዲያደርጉ መበረታታት አለባቸው።

ሪፖርቶቹ፣ ማንነታቸውን-ሳይገለጽ ሊደረጉ ይችላሉ፤ ነገር-ግን በርዕሰ-መምህሩ ወይም በርዕሰ-መምህሩ ተወካይ - ማንነታቸው ባልታወቀ ሪፖርት ላይ ብቻ-መሠረት አድርጎ፣ የዲሲፕሊን እርምጃ ሊወሰድ አይችልም፤ ሆኖም-ግን እንዲህ ዓይነቱ ሪፖርት ምርመራን-ሊያነሳሳ ይችላል።

DCPS፤ በተለያዩ ቋንቋዎች የሚገኙ የሪፖርት ማቅረቢያ ቁሳቁሶች/materials መኖራቸውን፣ እና ስለሪፖርት ማቅረቢያ መረጃ በተለያዩ አቀማመጣቸው - ለተማሪዎች እና ለቤተሰቦች በትምህርት ቤቱ እንዲዳረስ ያደርጋል። ክስተቶችን ሪፖርት-ለማድረግ፣ በ‘OYE’ ውስጥ የሚገኘው የዲስፕሊን እና የትምህርት ቤት ባህል ዳይሬክተር - በDCPS ማዕከላዊ ቢሮ (Central Office)፣ 1200 First Street, NE, 8th Floor, Washington, DC 20002 ውስጥ እንደሚያደርገው-ሁሉ፤ እያንዳንዱ የትምህርት ቤት ርዕሰ-መምህር ወይም የርዕሰ-መምህር ተወካይ፣ እገዛ-ለማድረግ የሚገኙ-ይሆናል።

## ሪፖርት-የማድረጊያ ሂደቶች

1. ሁሉም ሪፖርቶች፤ በDCPS የተፈቀደውን የማንጓጠጥ ክስተት ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽን - በመጠቀም መፃፍ አለባቸው። አባሪ (Appendix) B
2. ሪፖርቶች፤ በርዕሰ-መምህሩ ወይም በርዕሰ-መምህሩ ተወካይ ወዲያውኑ መመርመር አለባቸው።
3. የርዕሰ-መምህሩ ወይም የርዕሰ-መምህሩ ተወካይ፣ የማንጓጠጥ ድርጊቱን ማን-እንደፈፀመው እና ሌሎች በድርጊቱ-ውስጥ የተሳታፊነት ሚና እንደተጫወቱና እንዳልተጫወቱ የማረጋገጥ-እርምጃዎችን በመውሰድ፣ ማንጓጠጡ በትክክል-መፈጸሙንና-አለመፈጸሙን ይወስናል።
4. የተጠቂውን እና የማንኛውንም ምስክሮች፣ እምነት እና ልበ-ሙሉነት ለማሳደግ ጥረት መደረግ አለበት።
5. ርዕሰ-መምህሩ ወይም የርዕሰ-መምህሩ ተወካይ፣ የተጠቂው እና የጥቃት-አድራሹን ወላጆች/አሳዳጊዎች - ያሳውቃል።
6. ርዕሰ-መምህሩ ወይም የርዕሰ-መምህሩ ተወካይ፣ በ‘Chapter 25’ ውስጥ በተዘረዘረው መሠረት፣ ከፍትህ-ሂደት መብቶች ጋር አብረው-የሚሄዱ፣ የሚያስከትሉትን-ቅጣቶች እና/ወይም ጣልቃ-ገብነቶችን፣ በስራ-ላይ ያውላል።

7. ርዕሰ-መምህሩ ወይም የርዕሰ-መምህሩ ተወካይ፤ ስለ ክስተቱ፣ ስለተወሰዱት የዲሲፕሊን እርምጃዎች፣ እንዲሁም ከተጠቂው፣ ከምስክሮች እና ከጥቃት-አድራሹ የተሰጡትን መግለጫዎችን፣ በጽሁፍ ያዘጋጃል።

## XII. የማንጓጠጥ ክስተቶች ላይ፣ ምርመራ-ማድረግ

ስለ አንድ-ክስተት ምርመራ ከመደረጉ በፊት፣ ርዕሰ-መምህሩ ወይም የርዕሰ-መምህሩ ተወካይ፣ ሪፖርት በተደረገው የማንጓጠጥ ክስተት ላይ ጥቃት-ደርሶበታ ተብሎ-የተጠቀሰውን ተጎጂ - ደህንነቱ-የተጠበቀ መሆኑን - ለማረጋገጥ እርምጃዎችን ይወስዳል። እነዚህ እርምጃዎች፤ የተጎጂውን የደህንነት-ስሜቱ ወደነበረበት ለመመለስ እና አስፈላጊ-ከሆነ ደግሞ፣ ከተጨማሪ አደጋዎች እነርሱን ለመጠበቅ፣ የተቀረጹ ይሆናሉ። የእንደዚህ ዓይነት እርምጃዎች ምሳሌዎች፤ ተጎጂውን “ደህንነቱ የተጠበቀ/safe” ሰው-ሆኖ እንዲያገለግል የሠራተኛ-አባልን መመደብ፣ ተጠርጣሪ-የሆነውን አንጓጣጭ/አንጓጣጮችን የሚቀመጡበትን ቦታ  ወይም የጊዜ-ሰሌዳ በመቀያየር - ተጎጂውን የሚያገኙበትን ሁኔታ እንዲቀንስ ማድረግ ወይም ተጠቂ-ነው ተብሎ ከተጠረጠረው ጋር ምክክር-በማድረግ የደህንነት-ዕቅድን መፍጠርን - ያካትታሉ። አንድ-ጊዜ ምርመራው-ከተጠናቀቀ በኋላ፣ ተጎጂውን ከተጨማሪ የማንጓጠጥ ወይም የበቀል ድርጊቶች በመጠበቅ - ቀጣይ-የሆነ ደህንነቱን ለማረጋገጥ፣ እንደየ-አስፈላጊነቱ ተጨማሪ እርምጃዎች የሚወሰዱ-ይሆናል።

ርዕሰ-መምህሩ ወይም የርዕሰ-መምህሩ ተወካይ አንድ-ጊዜ የማንጓጠጥ ሪፖርቱን ከተቀበሉ-በኋላ፣ እንደየአስፈላጊነቱ - የሚከተሉት ቡድኖች እንዲያውቁት-ይደረጋል:

- <u>ወላጆች እና አሳዳጊዎች</u>: ርዕሰ-መምህሩ ወይም የርዕሰ-መምህሩ ተወካይ፤ ስለ ክስተቱ ሁኔታ እና ለዚህም ምላሽ-ለመስጠት በቦታው-ስለተቀመጡት ሂደቶች እና እርምጃዎች - ለተጠቂዎቹ፣ አንጓጣጮቹ፣ እና ተገቢ-ከሆነ ደግሞ ለምስክሮቹ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች፣ የሚያሳውቅ-ይሆናል። ርዕሰ-መምህሩ ወይም የርዕሰ-መምህሩ ተወካይ፤ ለወላጆችን ወይም አሳዳጊዎች - የክስተቱ ምርመራ ከመደረጉ በፊት ወይም በኋላ  ማሳወቅ-እንዳለባቸው የሚወስኑ-ይሆናል።

- <u>ሕግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች</u>: ርዕሰ-መምህሩ ወይም የርዕሰ-መምህሩ ተወካይ፤ ሪፖርት-የተደረገው ክስተት የወንጀል ድርጊትን ወይም የወንጀል ክሶችን ሊያካትት እንደሚችል ከወሰነ፣ ስለ ክስተቱ ያለውን-መረጃ - ለሚመለከተው የህግ አስከባሪ ባለስልጣናት መቅረብ አለበት። ይህን ውሳኔ እንደሚያደርግ አንዱ-አካል በመሆን - ርዕሰ-መምህሩ ወይም የርዕሰ-መምህሩ ተወካይ፣ ከህግ አስከባሪ ወይም የህግ አማካሪ ጋር መማከር ሊፈልጉ-ይችሉ ይሆናል። የሕግ አስከባሪውን-ማነጋገር የሚቻልበት ብቸኛ-አማራጭ የሚሆነው፣ ሁሉም ሌሎች መፍትሄዎች ተደርገው-ካልተሳኩ ብቻ ነው።

ርዕሰ-መምህሩ ወይም የርዕሰ-መምህሩ ተወካይ፤ እነዚህን የማንጓጠጥ ድርጊቶች ቡድኖችን፣ በህግ በሚፈቅደው መጠን ብቻ የሚያሳውቅ ይሆናል። ማስታወቂያው-የሚካሄደው፣ ለተጠቂዎች እና ለአንጓጣጮች  አገልግሎቶቹ መሰጠቱን ለማረጋገጥ እና ተጠቂዎችን ከተጨማሪ ወይም ቀጣይነት-ካለው ጥቃት ለመጠበቅ ብቻ ነው። ርዕሰ-መምህሩ ወይም የርዕሰ-መምህሩ ተወካይ፤ የማንጓጠጥ ክስተቶቹን ሪፖርት የሚያደርጉትን ማንነት-በሚስጢራዊነት ለመጠበቅ ሁሉንም-ጥረት ያደርጋል።

ርዕሰ-መምህሩ ወይም የርዕሰ-መምህሩ ተወካይ፤ የማንጓጠጥ ሪፖርቶችን ለመመርመር ኃላፊነት አለበት። የማንጓጠጥ ሪፖርቱ ከደረሰ ከአንድ-ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ፣ ስለ ክስተቱ ምርመራ ይጀመራል፤ እና ሪፖርቱ ከደረሰው ከ30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ - ይጠናቀቃል።

የምርመራው አካል-ሆኖ፣ ርዕሰ-መምህሩ ወይም የርዕሰ-መምህሩ ተወካይ - ተጠቂዎችን፣ አንጓጣጮችን፣ ምስክሮችን፣ ሠራተኞችን፣ ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን ጨምሮ - ማንኛውንም ተሳታፊ ወይም የሚመለከታቸው አካላትን ቃለ-መጠይቅ ያደርጋል።

ርዕሰ-መምህሩ ወይም የርዕሰ-መምህሩ ተወካይ፤ በተቻለ-መጠን ሚስጥራዊነትን ለሚመለከታቸው አካላት - እንደ የምርመራው አካል የሚሰጡ፣ እና ሁሉንም የሚመለከታቸው አካላት የማንጓጠጥ ድርጊቶችን ሪፖርት በማድረግ የበቀል-እርምጃ መውሰድ - የተከለከለ መሆኑን ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል። በDCPS ውስጥ የማንጓጠጥ ባህሪያትን የበለጠ-ትክክለኛ ምስል ለማመንጨት-እንዲቻል ለማድረግ፣ የምርመራው ሂደት - የተፃፉ መዝገቦች ተጠብቀው-የሚቆዩ እና የመከላከያ ዳታቤዝ/database ውስጥ ሊካተቱ ይችላሉ። አስፈላጊ-በሆነበት ቦታ፣ የሕግ አማካሪዎችን ምክር-የሚያካትት ድንጋጌዎች ይደረጋሉ።

የማንጓጠጥ ክስተትን በሚመረመርበት ጊዜ፣ ርዕሰ-መምህሩ ወይም የርዕሰ-መምህሩ ተወካይ - ሪፖርት-የተደረገው ክስተት፣ ከግጭት ይልቅ - የጥቃት ሰለባ፣ የማንጓጠጥ ምልክት-የሚታይበት መሆኑን ለማረጋገጥ-መጣር ያስፈልገዋል። ሪፖርት-የተደረገውን ክስተት በሚመረመርበት ጊዜ-ላይ፣ ርዕሰ-መምህሩ ወይም የርዕሰ-መምህሩ ተወካይ - የተከሰተውን ክስተት ለማስቆም እና ለወደፊቱ እንደዚህ ያሉ ሁኔታዎችን ለመከላከል፣ ተጎጂው ምን የመረጃ-ምንጮች እንደነበሩት እና ማግኘት-እንደቻለ፣ ተጠቂውን ቃለ-መጠይቅ በማድረግ - ለመወሰን ሙከራ-ያደርጋል። የተጠቂው ሪፖርቶች - ጥቂት ወይም ምንም የመረጃ-ምንጮች - ክስተቱን ለማቆም ወይም የወደፊት-ሁኔታዎች ገንቢ-በሆነ መንገድ ማስተናገድ የማይችል ከሆነ፤ ይህ-መረጃ እንደ አስገዳጅ ሆኖ የሚያገለግል-ሲሆን፣ ምንም እንኳን መደምደሚያ ባይሆንም-እንኳ፣ ሪፖርት-የተደረገው ክስተት የማንጓጠጥ ክስተት መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ነው።

ርዕሰ-መምህሩ ወይም የርዕሰ-መምህሩ ተወካይ - ሪፖርት-የተደረገው ክስተት የማንጓጠጥ ጉዳይ ስለመሆኑና-አለመሆኑ ለመወሰን፣ ውሳኔዎችን በማድረግ ክስ ይመሰረትበታል። እነዚህ ውሳኔዎች፤ አጠቃላይ-የሆኑ እውነታዎችን እና ከክስተቱ-ጋር የተያያዙ ሁኔታዎችን - ከግምትውስጥ በማስገባት ነው። ርዕሰ-መምህሩ ወይም የርዕሰ-መምህሩ ተወካይ - የማንጓጠጥ ክስተት መከሰቱን ከወሰነ፣ እርሱ/ሷ ክስተቱ እንዳይደገም ለመከላከል እና የተጠቂውን ደህንነት-ወደነበረበት ለመመለስ፣ የአስፈጻሚነት እርምጃዎችን መውሰድ አለበት።

ርዕሰ-መምህሩ ወይም የርዕሰ-መምህሩ ተወካይ - ጥልቅ-የሆነ እና ፍትሃዊ-የሆነ ምርመራ ለማካሄድ፣ ተጨማሪ ድጋፍ እንደሚያስፈልግ ከወሰነ፤ በታዳጊ-ወጣት ተሳትፎ ቢሮ/Office of Youth Engagement - ውስጥ የሚገኙትን፣ የዲሲፕሊን እና የትምህርት ቤት ባህል ዳይሬክተርን ያነጋግራል።

## XIII. ከበቀል-እርምጃ - መከላከል

የትምህርት ቤቱ ርዕሰ-መምህር ወይም የርዕሰ-መምህሩ ተወካይ፤ ማንኛውንም ሰው - ተማሪ ወይም ተማሪ-ያልሆነን፣ ተከሳሽ ወይም ከሳሽን፣ ወዘተ... በቀልን ሪፖርት-ሲያደርጉ፣ ፋይል-ሲያደርጉ ወይም አቤቱታ-ሲያቀርቡ - ለአቤቱታው ተጠያቂ ናቸው፤ ወይም በምርመራ ላይ የDCPS ማንጓጠጥን መከላከል ፖሊሲን መጣስ - በሚመለከት ከሚደረገው እርምጃ ለመጠበቅ፤ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል። ሠራተኛ፣ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች ወይም ተማሪ፤ በቅን-ልቦና ስለ አንድ ክስተት ወይም መረጃ - በዚህ መመሪያ መሠረት፣ ማንጓጠጥን ሪፖርት ያደረገ፤ ከሪፖርቱ ለሚደርስ ጉዳት ከሚደርስበት እርምጃ ነፃ-የሚሆን፣ መሆን አለበት።
የማስፈራሪያ-ዛቻ ወይም የበቀል እርምጃ፣ ከሰው-ወደ-ሰው፣ በኤሌክትሮኒክ/electronic መንገድ፣ ወይም በሦስተኛ ወገኖች በኩል የሚደርስ-ሆነም አልሆነ፤ ጥሰቱን-ያደረገውን - ለዲሲፕሊን እና ሌሎች የእርምት-እርምጃዎች የሚወሰዱ - ከባድ ጥፋቶች ናቸው፤ ይህም የረጅም ጊዜ እገዳን፣ እንዳይገባ-ማድረግ ወይም መባረርን ያካትታል።

## XIV. መደበኛ-የሆነ - አቤቱታዎች/Complaints እና ቅሬታዎች/Appeals

ከማንጓጠጥ ወይም ትንኮሳ ጋር የተያያዘ መደበኛ-የሆነ ቅሬታ ማቅረብ የሚፈልጉ ወገኖች፣ ወይም ስለ ማንጓጠጥ ወይም ትንኮሳ ክስተቱ በDCPS በተደረገው ውሳኔ ላይ፣ በDCPS የመጀመሪያው የምርመራ ውጤት-ላይ ባለመርካታቸው ምክንያት - የይግባኝ-አቤቱታ ለማቅረብ የሚፈልጉ፣ በ5---B DCMR § 2405 ወይም የሦስተኛ-ወገን የቅሬታ ሂደቶች በያዘው 5---E DCMR § 405 ውስጥ - ባለው-መሠረት ማቅረብ-ይችላሉ። የእነዚህ የቅሬታ ሂደቶች ቅጂ/copy - በአባሪ (Appendix) ውስጥ የሚገኝ-ነው። በተጨማሪም፤ መደበኛ-የሆነ ቅሬታን እንደተቀበሉ፣ ተቀባዩ-አካል በዲሲ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ (DC Human Rights Act) መሠረት፣ ተጨማሪ-የሆነው ትክክለኛ-ነገርን ለማግኘት፣ በሚችሉት-አቅም፣ ለሚያቀርበው አካል ማሳወቅ አለበት።

የተከሳሽ-ወገኖች - ተከሰተ-በተባለው ማንጓጠጥ ወይም ትንኮሳ ላይ-በተሰጠው የዲሲፕሊን እርምጃ ውጤት አጥጋቢ-ሆኖ ያላገኙት ወገኖች፤ ውሳኔውን በ'Chapter 25' በተማሪው የዲሲፕሊን ይግባኝ ሂደት አማካኝነት - የአቤቱታ-ይግባኝ ማለት ይችላሉ፤ ይህም በአባሪ/Appendix ውስጥ የሚገኝም-ይሆናል።

# አባሪ

## አባሪ (APPENDIX) A: የመረጃ-ምንጭ ማገናኛዎች/Resource Links

**Mayor's Bullying Prevention Model Policy**
*ohr.dc.gov/Bullyingprevention.policy*

**D.C. Municipal Regulations**
*dcregs.dc.gov*

**DCPS Chapter 25 Student Discipline Policy**
*dc.gov/DCPS/Files/downloads/In---the---Classroom/DCPS---**Chapter**---**25**---Tiers*

**U.S. Department of Health and Human Services**
*stopBullying.gov*

**Pacer's National Health Bullying Prevention Center**
*Pacer.org/Bullying/*

**Health Education Resources of the Office of the State Superintendent of Education (OSSE)**
http://psse.dc.gov/service/health---education---resources

**The Anti---Defamation League – Combat Bullying Tools and Resources**
*adl.org/combatBullying/*

**Olweus Bullying Prevention**
*Violencepreventionworks.org/public/olweus*

# አባሪ (APPENDIX) B: የማንጓጠጥ ክስተት ሪፖርት-የማድረግ፣ የDCPS ምሳሌ

## የግል መረጃ/Personal Information

1. (በምርጫ-የሚደረግ/Optional) ሪፖርቱን የሚያጠናቅቀው ሰው ስም_______________________________________
የማንጓጠጥ ሪፖርት፣ማንነትን-ሳይገለጹ መደረግ እንደሚችል እባካችሁ አስታውሱ። ሆኖም-ግን፣ ማንነትንም-ሳያሳውቁ በተደረገ ሪፖርት-ላይ ምላሽ-በመስጠት ብቻ፣ ምንም-ዓይነት የዲሲፒሊን እርምጃ አይወሰድም። ሪፖርቱ፤ የዲሲፒሊን እርምጃ ለመውሰድ፣ አስፈላጊ-የሆኑ ተጨማሪ መረጃዎች ላይ ምርመራ ለማድረግ፣ መሠረት-ሊሆን ይችላል።

2. እናንተ፤ የሚከተለው ናችሁ:
a. የዚህ ባህሪይ - ተጠቂ/Victim: ________________________________
b. ለክስተቱ ምስክር-የሆነ: ________________________________

3. እናንተ፤ የሚከተለው ናችሁ:
a. ተማሪ ________________________________
b. ወላጅ/አሳዳጊ ________________________________
c. የሠራተኛ አባል (እባካችሁ ግለጹ): ________________________________
d. ሌላ (እባካችሁ ግለጹ): ________________________________

4. (በምርጫ-የሚደረግ/Optional) የእናንተ የመገኛ-አድራሻ መረጃ:
a. ስልክ: ________________________________
b. ኢሜል፡ ________________________________

## የክስተቱ መረጃዎች

የተጠቂው/victim ስም(ሞች):

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

የአንጓጣጩ (bully) ስም(ሞች):

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

## የክስተቱ ቀን እና ሰዓት

# አባሪ/Appendix C---የተማሪ የቅሬታ-ሂደት/Grievance Procedure

2405.1 በዚህ ክፍል/section ውስጥ-የተቀመጠው የቅሬታ ሂደት (grievance procedure)፣ ለሚከተሉት ሕጎችን በመጣስ ለሚጠረጠሩት ለማንኛውም- ቅሬታዎች ወይም አቤቱታዎች በስራ-ላይ ይውላል:

(a) 'Section 504 of the Rehabilitation Act of 1973'፤ በጉዳተኝነት-ላይ መሠረት አድርጎ-የሚደረግ አድልዎን የሚከለክል፤

(b) 'Title II of the Americans with Disabilities Act of 1990'፤ ይህም -በጉዳተኝነት-ላይ መሠረት አድርጎ-የሚደረግ አድልዎን የሚከለክል፤

(c) 'Title IX of the Education Amendments of 1972'፤ በፆታ-ላይ መሠረት አድርጎ-የሚደረግ አድልዎን የሚከለክል፤

(d) 'Title VI of the Civil Rights Act of 1964'፤ በዘር፣ በቀለም እና በብሄራዊ የማንነት-መነሻ ላይ መሠረት አድርጎ-የሚደረግ አድልዎን የሚከለክል፤

(e) 'የኮሎምብያ ዲስትሪክት የሰብዓዊ-መብቶች ሕግ/District of Columbia Human Rights Law, Title 2, Chapter 14 of the D.C. Official Code'፤ በዘር፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በብሄራዊ የማንነት-መነሻ፣ በፆታ፣ ዕድሜ፣ በትዳር-ሁኔታ፣ በየግል-አቀራረብ/personal appearance፣ በፆታዊ እውቅና፣ የጾታ መለያ ወይም አገላለጽ፣ በቤተሰባዊ-ሁኔታ፣ በቤተሰብ ኃላፊነቶች፣ በፖለቲካ አመለከካከት፣ በገቢ-ምንጭ፣ እና በጉዳተኝነት-ላይ መሠረት ያደረገን አድልዎ የሚከለክል፤ ወይም

(f) 'The Age Discrimination Act of 1975'፤ በዕድሜ-ላይ መሠረት አድርጎ-የሚደረግ አድልዎን የሚከለክል፤

2405.2 በዚህ ክፍል/section ውስጥ-የተቀመጠው የቅሬታ ሂደት (grievance procedure)፣ በሚከተሉትን-ሁኔታዎች ውስጥ ለሚቀርቡት ሁሉም ቅሬታዎች ወይም አቤቱታዎች በስራ-ላይ የሚውሉም-ይሆናል:

(a) ማንኛውም ተማሪ ወይም የተማሪዎች ቡድን፣ አጥጋቢ-የሆነ ትምህርታዊ ዕድሎችን ከማግኘት ተከልክለዋል የሚል-ክስ በሚኖርበት ጊዜ፤

(b) የተማሪዎች መብቶች፣ ወይም የማንኛውም ግለሰብ ተማሪ - ተከልክለዋል ወይም ተቆርጧል የሚል-ክስ በሚኖርበት ጊዜ፤

(c) ማንኛውም ተማሪ ወይም የተማሪዎች ቡድን - በዘፈቀደ ወይም ተገቢ-ባልሆነ ደንብ፣ ሂደት፣ ወይም የፀባይ መደበኛነት/standard of conduct ውስጥ አላግባብ ተጠቂ ሆኗል የሚል-ክስ በሚኖርበት ጊዜ፤

(d) ማንኛውም ተማሪ ወይም የተማሪዎች ቡድን - ተማሪው-ብቁ በሆነባቸው በማንኛውም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ውስጥ ለመካፈል ተከልኳል የሚል-ክስ በሚኖርበት ጊዜ፤

(e) ተማሪው፣ የማንጓጠጥ (bullying) ወይም ትንኮሳ ተጠቂ በሚሆንበት-ጊዜ - የወሲባዊ ትንኮሳ (sexual harassment)ን ጨምሮ፤ እና

(f) በዚህ 'title' ውስጥ የተለየ የቅሬታ ሂደት ወይም የፍርድ-ቤት ተሰሚነት ሂደት (hearing process) በሌለው በሕግ-የተሰጠውን መብት የሚጣስ ሌላ ማንኛውም ዓይነት-ነገር።

2405.3 ከትምህርት ቤት የታገደ ወይም የተባረረ ተማሪ፣ በዚህ ክፍል/section መሠረት - ቅሬታ ማቅረብ የለበትም፣ ነገር-ግን በ'chapter B 25፤ ባለው አሰራር-መሰረት የይግባኝ-ጥያቄ ማቅረብ ይችላል።

2405.4 በ § B 2405.1 ወይም B 2405.2 ላይ-በተቀመጠው-መሠረት - በተፈጠረ-ጉዳይ ላይ ቅሬታን-የሚያቀርብ ግለሰብ፤ በዚህ ክፍል/section ውስጥ የተካተተውን ሂደት-መከተል አለበት። በማንጓጠጥ ወይም በትንኮሳ - የወሲብ ትንኮሳን ጨምሮ - ተጠቂ-የሆነ ግለሰብ፣ እነዚህን ሂደቶች ወይም በ§ B 2405.5 ውስጥ ያሉትን ሂደት ሊከተል-ይችላል። በዚህ 'Chapter' ውስጥ § B 2401.15ን በተከተለ-ሁኔታ፣ ቅሬታው - ተማሪውን ወክሎ በወላጅ ወይም በአሳዳጊው ፋይል-ሊደርግ ይችላል።

(a) ቅሬታውን የሚያቀርበው ግለሰብ (ቅሬታ-አቅራቢ/the grievant)፣ ለርዕሰ-መምህሩ ወይም ለሌላ ለፕሮግራሙ ወይም እንቅስቃሴው ኃላፊ-ለሆነ - የትምህርት ቤቱ ሹም፣ ኢ-መደበኛ የሆነ አቤቱታ ሊያቀርብ-ይችላል። ቅሬታ-አቅራቢው፤ ከርዕሰ-መምህር ወይም ለፕሮግራሙ ወይም እንቅስቃሴው ኃላፊ ለሆነ ሹም-ሣይሆን - ለአስተማሪ ወይም አስተዳደር አቤቱታውን የሚያቀርብ ከሆነ፤ ያ-ሰው፣ ስለ አቤቱታው ምንነት፣ ለርዕሰ-መምህር ወይም ለፕሮግራሙ ወይም እንቅስቃሴው ኃላፊ ለሆነ ሹም ማሳወቅ-ያስፈልገዋል።

(b) ርዕሰ-መምህሩ - ለቅሬታ-አቅራቤው ተጠያቂ-ሆነው የቀረቡ-ከሆነ ወይም በቅሬታው ዙሪያ ባሉ ሁኔታዎች ውስጥ የተካፈሉ-ከሆኑ፤ ቅሬታ-አቅራቢው - በርዕሰመምህሩ ትምህርት ቤት ላይ ስልጣን ላለው የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ (Instructional Superintendent)፣ ኢ-መደበኛ ቅሬታ ማቅረብ አለበት።

(c) ኢ-መደበኛ ቅሬታን የተቀበለው ሰው፤ በኢ-መደበኛ በሆነ መንገድ ችግሩን መርምሮ ለመፍታት መሞከር ያለበት ሲሆን - እነዚህ ጨምሮ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ ሣይወሰን - በስብሰባዎች፣ ኮንፈረንሶች እና ውይይቶች አማካኝነት መፍታት-አለበት። ግለሰቡ፤ ጉዳዩን ለመመርመር የተወሰዱ እርምጃዎችን ሁሉ - በጽሁፍ የሰነድ ማስረጃ ማቅረብ አለበት።

(d) ኢ-መደበኛ ሂደት ላይ የውሳኔ ሃሳብ ወይም ውሳኔውን፣ በዳይሬክተሩ ወይም በሌላ የትምህርት ቤት ባለስልጣን፣ ለቅሬታ አቅራቢው - ኢ-መደበኛ ቅሬታውን ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በአስር (10) የትምህርት ቀናት ውስጥ - ውሳኔ-ይሰጣል።

(e) በተሰጠው ውጤቱ ያልተደሰተ ወይም ላለመጠቀም የመረጠ -- ኢ-መደበኛ የሆነ ሂደትን፣ ቅሬታ-አቅራቢ የሆነው፣ ለርዕሰ-መምህሩ ወይም ለሌላ ኃላፊነት ላለው የትምህርት ቤት ባለስልጣን - በጽሁፍ ቅሬታ ማቅረብ ይችላል። የጽሁፍ ቅሬታዎች፤ ክስተቱ ወይም የቅሬታ ሁኔታው ከደረሰ - በአርባ አምስት (45) የቀን-መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ወይም ኢ-መደበኛ ሂደት በተጠናቀቀ በአስር (10) የቀን-መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ - ማንኛውም-ካለ፣ ከሁለቱ-በረዘመው ቀን፤ መቅረብ አለበት። የማስገቢያው የጊዜ-አቀማመጦች የሚተመኑት፣ ቅሬታ-አቅራቢው ትንኮሳውን ያልተገነዘበው ወይም የማያውቅ ሆኖ-በሚገኝበት ጊዜ-ነው።

(f) ሁሉም የአቤቱታ-ቅሬታዎች፣ የሚከተሉትን መረጃዎች - በቅሬታ-አቅራቢው ሊታወቅ እስከሚችለው ድረስ፣ ማካተት-አለበት:

(1) ስም፣ ክፍል እና ተማሪው-የሚማርበት ትምህርት ቤት፤

(2) ክስተቱ-የተፈጸመበት ቀን፣ በግምት-ምን ሰዓት ላይ እንደሆነ፣ እና ቦታው፤

(3) በክስተቱ-ላይ የነበረውን፣ የማንጓጠጥ ወይም ትንኮሳ ዓይነት፤

(4) ትንኮሳ-ነው ተብሎ-የተወሰደውን ድርጊቶች የፈጸመውን ሰው(ዎች) የመለየት-ሂደት፤

(5) ተከስቷል-የተባለው ትንኮሳ ወደ ሌላ ሰው(ዎች) ላይ ያነጣጠረ ከሆነ፣ የእነዚህ ሰዎች ማንነት፤

(6) ማንኛውም ምስክሮች በቦታ-የነበሩ መሆንና-አለመሆኑን፣ እና የእነርሱን ማንነት፤ እና

(7) ማንኛውም የቃል-መግለጫዎች ወይም አካላዊ ግንኙነትን ጨምሮ፣ ስለ ክስተቱ የተለየ እውነታዊ-ሁኔታን መግለጫ።

(g) ርዕሰ-መምህሩ ወይም ለሌላ ኃላፊነት ላለው የትምህርት ቤት ባለስልጣን፤ ከቅሬታ አቅራቢ(ዎች)፣ ተማሪዎች፣ ወላጆች፣ አስተማሪዎች፣ ሌሎች የትምህርት ቤት ሹሞች እና ሌሎች ተሳታፊ-የሆኑ አካላት ጋር - ኮንፈረንስ በማካሄድ እና አስፈላጊ-ሆኖ ሲገኝ ከህግ አማካሪ፣ ከ'Title IX' አስተባባሪ ወይም ከSection 504 አስተባባሪ ጋር-ሆኖ በመመካከር፣ መደበኛ ምርመራን በመጀመር፣ በጽሁፍ-የቀረበውን ቅሬታ ለመፍታት ይሞክራሉ። በተጨማሪም፤ ምርመራው - በአቤቱታ-አቅራቢው የቀረበውን ማንኛውንም መረጃ መመርመር እና ቅሬታ-አቅራቢው ለይቶ-ካቀረባቸው ምስክሮች ጋር ቃለ-መጠይቅ ማድረግን፣ ማካተት አለበት። ተገቢ-የሆነው የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ/Instructional Superintendent፤ ስለ ቀረበው ቅሬታ እና ምርመራ፣ በጽሁፍ ይነገራቸዋል እና ቅሬታውን ለመፍታት ርዕሰመምህሩ ወይም ሌላ የትምህርት ቤት ባለስልጣንን ማማከር ይችላሉ።

(h) የጽሁፍ ቅሬታውን የሚመረምሩት - ርዕሰ-መምህሩ ወይም ለሌላ ኃላፊነት ላለው የትምህርት ቤት ባለስልጣን፤ ለቅሬታ-አቅራቢው እና የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ/Instructional Superintendent - የጽሁፍ ምላሽ-ያቀርባሉ።

(i) የጽሁፍ ቅሬታው በደረሳቸው በአስር (10) የትምህርት ቀናት ውስጥ፣ የጽሁፍ ምላሽን ያቀርባሉ፤ ምርመራው ረዘም-ያለ ጊዜ የሚፈጅ-ከሆነ - ለቀረቡት-አካላት/parties - የዘገየበትን ምክንያት እና የሚገመተውን የጊዜ-አቀማመጥ ጨምሮ - እንዲያውቁት-ይደረጋል።

(j) ቅሬታ-አቅራቢው፤ በርዕሰ-መምህሩ ምላሽ ያልረኩበት-ከሆነ፣ ቅሬታ-አቅራቢው ተማሪው በሚማርበት ወይም ቅሬታው በተነሳበት ትምህርት ቤት ላይ - ስልጣን ላለው የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ/Instructional Superintendent - ይግባኝ ማቅረብ ይችላል። የመጀመሪያውን ምላሽ የሰጡት - የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ/Instructional Superintendent ከሆኑ፤ ቅሬታ-አቅራቢው፣ በቻንስለሩ ለተመደበ ሌላ የትምህርት ቤት ሹም - አቤቱታውን ፋይል ሊያደርግ ይችላል። አቤቱታው፤ በተቀበሉ ወይም ከመጀመሪያ ምላሽ ማስታወቂያው በአስር (10) የቀን-መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ፣ ፋይል ይደረጋል።

(k) የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ/Instructional Superintendent ወይም ለሌላ ተወካይ፤ የርዕሰ-መምህሩን ምርመራ እና ግኝቶች ላይ ምልከታ-በማድረግ፣ እና በቅሬታው ላይ ተጨማሪ ምርመራ

በማካሄድ - ሁሉንም ተሳታፊ አካላት/parties ያካተተ ስብሰባ ማድረግን እና አስፈላጊ-ከሆነ ከህግ አማካሪ ጋር መመካከርን-ጨምሮ፣ ቅሬታውን ለመፍታት ይሞክራሉ።

(l) ቅሬታውን በተቀበለ በአስር (10) የትምህርት ቀናት ውስጥ፣ የጽሁፍ ምላሽ የሚሰጥ-ይሆናል።

(m) ቅሬታ-አቅራቢው፤ በምላሹ ካልረካበት ወይም የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ/Instructional Superintendent ወይም ሌላ ተወካዩ - በቂ-ውሳኔን ማግኘት ካልቻሉ፤ ቅሬታ-አቅራቢው ወይም የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ/Instructional Superintendent ወይም ሌላ ተወካዩ - በጽሑፍ ምላሽ በተሰጠው በአስር (10) የቀን-መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ፣ ቅሬታውን - ተገቢ እና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት፥ በቅሬታ-አቅራቢው የምልከታ-ማድረጊያ ፓኔል (review panel) ፊት እንዲቀርብ መጠየቅ ይችላል። ፓኔሉ (The panel)፤ በቻንስለር ወይም ተወካዩ የተሾሙ - ሦስት (3) ሰዎችን ያቀፈ ሲሆን፣ የSection 504 አስተባባሪ፣ የ'Title IX' አስተባባሪ፣ ከDCPS የተገዢነት-ቢሮ ውስጥ ያሉ ግለሰቦች፣ የጠቅላይ ምክር ቤት ቢሮ፣ ሌሎች የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጆች/Instructional Superintendents ወይም የትምህርት ቤት ሹሞች እና ሌሎች በቅሬታ-አቅራቢው ስለተነሱት ጉዳዮች ከስልጠና እና እውቀት ጋር የሚገኙ ፍላጎት-የሌላቸውን ሰዎችን - የሚያካትት-ይሆናል።

(n) በምልከታ-ማድረጊያ ፓኔል (review panel) ፊት በሚቀርቡት ሁሉም ጉዳዮች-ውስጥ፤ ፓነሉ/panel - ለትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ/Instructional Superintendent፣ ወይም ሌላ ተወካይ፣ ከጽሁፍ ግኝቶች እና የውሳኔ ሃሳቦች ጋር - በትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ/Instructional Superintendent ወይም በሌላ ተወካይ እና ርዕሰ-መምህሩ - ሃሳብ-ለቀረበበት ተግባት፣ የሚያቀርብ ይሆናል። ግኝቶቹ እና የቀረቡት-ሃሳቦች፤ በፓነሉ (the panel) - በ§ B 2405.4 (m) ላይ የተጠቀሰውን በተቀበለ፣ በአስር (10) ቀናት ውስጥ፣ የሚሰጥ ይሆናል።

(o) ግኝቶቹ እና የውሳኔ-ሃሳቦቹ በደረሰበት - በአምስት (5) ቀናት ውስጥ፣ በትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ/Instructional Superintendent ወይም ሌላ ተወካይ፣ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሰጣሉ፤ ይህም የትምህርት ቤቱ ስርዓት የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሆናል። በትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ/Instructional Superintendent ወይም ሌላ ተወካይ፤ ስለ ውሳኔው ለቅሬታ-አቅራቢው፣ ለርዕሰ-መምህሩ እና አግባብ ከሆነ-ደግሞ፣ ለቅሬታ-አቅራቢው ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት።

(p) ቅሬታ-አቅራቢው፣ በተጨማሪም - አቤቱታውን በቀጥታ ከአሜሪካ የትምህርት መምሪያ፣ የሰው-ልጅ መብቶች ቢሮ (U.S. Department of Education, Office of Civil Rights) ጋር፤ በዚህ ክፍል/section ውስጥ ያሉትን ማንኛውም ሂደቶችን - ሳይጠቀም፣ ወይም ሳያጠናቅቅ - አቤቱታውን ፋይል ማድረግ ይችላል። ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት፣ በhttp://www.ed.gov/ocr/complaintprocess.html ላይ ተመልከቱ ወይም በ(202) 453---6020 ደውሉ።

(q) ቅሬታ-አሰሚው፣ አቤቱታውን በቀጥታ ከኮሎምቢያ ዲስትሪክት ኮሚሽን - በሰብዓዊ መብቶች (District of Columbia Commission on Human Rights)፣ በዚህ ክፍል/section ውስጥ የተካተቱትን ሂደቶች ሳይጠቀም፣ ፋይል ማድረግም ይችላል። ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት፣ በ http://www.ohr.dc.gov ላይ ተመልከቱ፣ ወይም በ(202) 727---4559 ደውሉ።

2405.5 የማንጓጠጥ ወይም የትንኮሳ ተጠቂ-የሆነ ቅሬታ-አቅራቢ፣ የወሲብ-ትንኮሳን ጨምሮ - በተቀጣሪ-ሠራተኛ፣ ተማሪዎች፣ ወይም በሦስተኛ-ወገኖች፤ በእርሱ ወይም በእርሷ አስተሳሰብ - የተፈጠረ አድርጎ ከወሰደ፣ የእርሱን ወይም የእርሷን አቤቱታ መፍትሄ ለመስጠት - ይህን ሂደት ለመከተል መምረጥ-ይችላሉ:

(a) የማንጓጠጥ ወይም የትንኮሳ ተጠቂ-የሆነ ግለሰብ፣ በቃል አቤቱታ-ማቅረብ ወይም በጽሁፍ - ለማንኛውም አስተማሪ፣ አስተዳዳሪ፣ ወይም ካውንስለር - ሊያቀርብ ይችላል።

(b) ቅሬታ-አቅራቢው - አቤቱታውን ወይም አቤቱታዋን በቃል-ካቀረበ/ች፤ አስተማሪው፣ አስተዳዳሪው ወይም ካውንስለሩ - ከቅሬታ-አቅራቢው ጋር ያደረጉትን ንግግር፣ በጽሁፍ ሪፖርት ማዘጋጀት አለባቸው። ቅሬታ-አቅራቢው በጽሁፍ አቤቱታዎችን ካቀረበ፣ በማንኛውም ዓይነት-አቀራረብ ሊሆን ይችላል። ሁሉም የአቤቱታ-ቅሬታዎች፣ የሚከተሉትን መረጃዎች - በቅሬታ-አቅራቢው ሊታወቅ እስከሚችለው ድረስ፣ ማካተት-አለበት:

(1) ስም፣ ክፍል እና ተማሪው-የሚማርበት ትምህርት ቤት፤

(2) ክስተቱ-የተፈጸመበት ቀን፣ በግምት-ምን ሰዓት ላይ እንደሆነ፣ እና ቦታው፤

(3) በክስተቱ-ላይ የነበረውን፣ የማንጓጠጥ ወይም ትንኮሳ ዓይነት፤

(4) ትንኮሳ-ነው ተብሎ-የተወሰደውን ድርጊቶች የፈጸመውን ሰው(ዎች) የመለየት-ሂደት፤

(5) ተከስቷል-የተባለው ትንኮሳ ወደ ሌላ ሰው(ዎች) ላይ ያነጣጠረ ከሆነ፣ የእነዚህ ሰዎች ማንነት፤

(6) ማንኛውም ምስክሮች በቦታ-የነበሩ መሆንና-አለመሆኑን፣ እና የእነርሱን ማንነት፤ እና

(7) ማንኛውም የቃል-መግለጫዎች ወይም አካላዊ ግንኙነትን ጨምሮ፣ ስለ ክስተቱ የተለየ እውነታዊ-ሁኔታን መግለጫ።

(c) በውስጡ የተካተቱት ሁሉም ቅሬታዎች እና መረጃዎች፣ በሕጉ በተደነገገው መጠን-መሠረት፣ በሚስጥራዊነት የሚያዝ ይሆናሉ።

(d) ቅሬታውን ሪፖርት ተከትሎ፣ የሚቀጥለው የትምህርት ቀን ማብቂያው-ሳያልፍ፣ ለርዕሰ-መምህሩ ሪፖርት መደረግ አለበት። አስተማሪው፣ አስተዳዳሪው ወይም ካውንስለሩ፤ ስለ ከባድ ወይም ስፋት-ስላለው የማንጓጠጥ ወይም የትንኮሳ - ቅሬታዎችን፣ ከትምህርት ቀን ማብቂያው-ሳያልፍ - የአቤቱታውን ሪፖርት፣ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።

(e) ማንኛውም ርዕሰ-መምህር፣ አስተዳዳሪ ወይም የማንጓጠጥ ወይም የትንኮሳ ቅሬታዎችን የመቆጣጠር ወይም የመመርመር ኃላፊነት ያለው ሌላ የትምህርት ቤት ሠራተኛ፤ በቅሬታው ውስጥ ከተካተቱ፣ ወይም ማንኛውም ተጨባጭ ወይም ይሆናል-ተግሎ የታሰበ የጥቅም-ማግኘት ግጭት ካለ፣ ቅሬታውን የሚቀርበው - ተማሪው በሚማርበት ትምህርት ቤት አጠቃላይ-ስልጣን ላለው የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ ስራ-አስኪያጅ/Instructional Superintendent ወይም ቅሬታው ለሚወሰደው-እርምጃ በተነሳበት-ላይ - ፋይል የሚደረግ-ይሆናል።

(f) ርዕሰ-መምህሩ፤ ሁሉም ቅሬታዎች በትክክል ተመርምረው በእነዚህ ሂደቶች መሠረት እንዲከናወኑ የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፤ ነገር-ግን የማንጓጠጥ እና የትንኮሳ ቅሬታዎችን ለማካሄድ ኃላፊነቱን-ለሌላ በመስጠት መወከል ይችላል። ርዕሰ-መምህሩ ወይም ተወካዩ፣ የሚከተሉትን እርምጃዎች ይወስዳል:

(1) በአንድ (1) የትምህርት-ቀን ውስጥ – ከሶቹን፣ ከቅሬታ-አድራጊው ጋር ሚስጥራዊ ውይይት-ለማድረግ የጊዜ-ሰሌዳ መያዝ እና ማጠናቀቅ። ይህን-መሰል ውይይት-በሚደረግበት ወቅት፣ የከሱን ርዕሰ-ጉዳይ ማሳወቅ ወይም እንዲቀርብ-ማድረግ የለበትም።

(2) በአስር (10) የትምህርት-ቀናቶች ውስጥ – ርዕሰ-መምህሩ ወይም ተወካዩ - ምርመራውን ያጠናቅቁ እና የማንጓጠጥ ወይም የትንኮሳ ውንጀላዎቹ መሠረታዊ-ስለመሆናቸው እና አለመኖናቸው የሚጠቁም የጽሁፍ ሪፖርት ያዘጋጃል፤ ምርመራው ረዘም-ያለ ጊዜ የሚፈጅ-ከሆነ - ለቀረቡት-አካላት/parties - የዘገየበትን ምክንያት እና የሚገመተውን የጊዜ-አቀማመጥ ጨምሮ - እንዲያውቁት-ይደረጋል። ምርመራው/The investigation፤ የሚገተሉትን ጉዳዮች ማካተት-ያለበት ሲሆን፣ ነገር-ግን በእነዚህ ብቻ የተወሰነ-አይደለም: 1) ከቅሬታ-አቅራቢው ጋር ቃለ-መጠይቅ ማድረግ፤ 2) ከተጠረጠረው ተጠቂ-ሰው ጋር ቃለ-መጠይቅ (ቅሬታ-አቅራቢው ካልሆነ)፣ 3) ትንኮሳውን ወይም ማንጓጠጡን ፈፅሟል ተብሎ ከተጠረጠረው ርዕሰ ጉዳይ(ዎች) ጋር የተደረገ ቃለ-ምልልስ፤ 4) በቅሬታው ላይ ስለተከሰሱት እውነታዎች እውቀት ካላቸው ሠራተኞች እና ሌሎች (ተማሪዎችን ጨምሮ) ቃለ-መጠይቆች (አቤቱታውን ባቀረበው ተማሪ የተገለጸውን ጨምሮ)፣ እና 5) ሁሉንም ተዛማጅ-የሆኑ መዝገቦች መገምገም (በቅሬታ-አቅራቢው የተገለጹትን ጨምሮ)። ሪፖርቱ፤ የምርመራውን ውጤት የሚያንፀባርቅ እና ለሁሉም የቅሬታው አካላት/parties -መቅረብ አለበት። ሪፖርቱ፤ ማንኛውንም ጣልቃ-ገብነት ወይም የዲሲፕሊን እርምጃዎችን ጨምሮ (በቤተሰብ የትምህርታዊ መብቶች እና ግላዊነት ድንጋጌ/Family Educational Rights and Privacy Act, 20 U.S.C. §1232g; 34 C.F.R. §99.1 *et seq*. በሚፈቀደው መጠን)፣ ማንኛውንም የተወሰዱ-የክትትል-ማድረጊያ እርምጃዎችን ወይም የሚወሰዱትን - ሊያካትት ይችላል።

(3) ቅሬታ-አቅራቢው በሪፖርቱ ውስጥ በተካተቱት ግኝቶች ወይም ድርጊቶች ያልረካበት ከሆነ፣ የርዕሰ-መምህሩ ሪፖርት፣ ተማሪው በሚማርበት ትምህርት ቤት አጠቃላይ-ስልጣን ላለው የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ ስራ-አስኪያጅ/Instructional Superintendent ወይም ቅሬታው ለሚወሰደው-እርምጃ በተነሳበት-ውስጥ በቀረበበት - በአስር (10) የቀን-መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ፣ ቅሬታ-አቅራቢው - የጽሁፍ ቅሬታውን ፋይል ሊያደርግ ይችላል። ይህን-መሠሉ ቅሬታ ፋይል-ከተደረገ፣ ሂደቱ በ§§ 2405.4(k)---2405.4(o) ላይ በተገለጸው-መሠረት በስራ-ላይ ይውላል።

(g) ቅሬታ-አቅራቢው፣ በተጨማሪም - አቤቱታውን በቀጥታ ከአሜሪካ የትምህርት መምሪያ፣ የሰው-ልጅ መብቶች ቢሮ (U.S. Department of Education, Office of Civil Rights) ጋር፤ በዚህ ክፍል/section ውስጥ ያሉትን ማንኛውም ሂደቶችን - ሳይጠቀም፣ ወይም ሳያጠናቅቅ - አቤቱታውን ፋይል ማድረግ ይችላል። ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት፣ በhttp://www.ed.gov/ocr/complaintprocess.html ላይ ተመልከቱ ወይም በ(202) 453---

(h) ቅሬታ-አሰሚው፣ አቤቱታውን በቀጥታ ከኮሎምቢያ ዲስትሪክት ኮሚሽን - በሰብዓዊ መብቶች (District of Columbia Commission on Human Rights)፣ በዚህ ክፍል/section ውስጥ የተካተቱትን ሂደቶች ሳይጠቀም፣ ፋይል ማድረግም ይችላል። ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት፣ በ http://www.ohr.dc.gov ላይ ተመልከቱ፣ ወይም በ(202) 727---4559 ደውሉ።

2405.6 የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ ስራ-አስኪያጁ የመጨረሻ-ውሳኔ፣ ለትምህርት ቤት ስርዓቱ - የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሆናል።

2405.7 የመጨረሻ ውሳኔው ቅጂዎች/Copies - ለሁሉም አካላት/parties

2405.8 የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ ስራ-አስኪያጁ የመጨረሻ-ውሳኔ ቅጂ/copy፤ ወደ ቻንስለሩ እና የትምህርት-ቤቶች ቺፍ/Chief of Schools - የሚላክ-ይሆናል።

2405.9 ከማንኛውም አስተማሪ ወይም የትምህርት ቤት ሹም፣ አቤቱታው - ለምንም-ዓይነት የበቀል ሁኔታ ተጠቂ-መሆን የለበትም። ቅሬታ-አቅራቢ፤ በተማሪዎች፣ በአስተማሪዎች ወይም በሠራተኞች የሚደርስበትን በቀል - ቅሬታ-ለማቅረብ፣ እነዚህን ሂደቶች ሊጠቀም ይችላል።

## አባሪ/Appendix D---የሦስተኛ-ወገን የቅሬታ ሂደት/Third Party Grievance Procedure (ወላጆችን ጨምሮ)

405.1 በዚህ ክፍል/section ውስጥ-የተቀመጠው የቅሬታ ሂደት (grievance procedure)፣ ለሚከተሉት ሕጎችን በመጣስ ለሚጠረጠሩት ለማንኛውም- ቅሬታዎች ወይም አቤቱታዎች በስራ-ላይ ይውላል:

(a) ‘Section 504 of the Rehabilitation Act of 1973’፤ በጉዳተኝነት-ላይ መሠረት አድርጎ-የሚደረግ አድልዎን የሚከለክል፤

(b) ‘Title II of the Americans with Disabilities Act of 1990’፤ ይህም -በጉዳተኝነት-ላይ መሠረት አድርጎ-የሚደረግ አድልዎን የሚከለክል፤

(c) ‘Title IX of the Education Amendments of 1972’፤ በፆታ-ላይ መሠረት አድርጎ-የሚደረግ አድልዎን የሚከለክል፤

(d) ‘Title VI of the Civil Rights Act of 1964’፤ በዘር፣ በቀለም እና በብሄራዊ የማንነት-መነሻ ላይ መሠረት አድርጎ-የሚደረግ አድልዎን የሚከለክል፤

(e) ‘የኮሎምብያ ዲስትሪክት የሰብዓዊ-መብቶች ሕግ/District of Columbia Human Rights Law, Title 2, Chapter 14 of the D.C. Official Code’፤ በዘር፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በብሄራዊ የማንነት-መነሻ፣ በፆታ፣ ዕድሜ፣ በትዳር-ሁኔታ፣ በየግል-አቀራረብ/personal appearance፣ በፆታዊ እውቅና፣ የጾታ መለያ ወይም አገላለጽ፣ በቤተሰባዊ-ሁኔታ፣ በቤተሰብ ኃላፊነቶች፣ በፖለቲካ አመለከካከት፣ በገቢ-ምንጭ፣ እና በጉዳተኝነት-ላይ መሠረት ያደረገን አድልዎ የሚከልክል፤ ወይም

(f) ‘The Age Discrimination Act of 1975’፤ በዕድሜ-ላይ መሠረት አድርጎ-የሚደረግ አድልዎን የሚከለክል፤

405.2 በዚህ ክፍል/section ውስጥ የተቀመጠው የቅሬታ ሂደት አሰራር፣ ከኮሎምብያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (District of Columbia Public Schools) ተማሪ ወይም ሠራተኛ በስተቀር - በማንኛውም ግለሰብ ለሚቀርቡ ቅሬታዎች ተፈጻሚ-ይሆናል። ይህ የሚያካትተው - ነገር-ግን በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን - ለወላጆች፣ አሳዳጊዎች፣ እና የትምህርት ቤት ጎብኚ-እንግዶችን ያካትታል። በተማሪዎች ላይ የሚነሱ ቅሬታዎች እና አቤቱታዎች፤ በዚህ ‘Title’ Chapter B 24 ውስጥ በተካተቱት ሂደቶች መመራት አለባቸው። በሠራተኞች ላይ የሚነሱ ቅሬታዎች እና አቤቱታዎች፤ በዚህ ‘Title’ Chapter E 8 ውስጥ በተካተቱት ሂደቶች መመራት አለባቸው።

405.3 በዚህ ክፍል/section ውስጥ-የተቀመጠው የቅሬታ ሂደት (grievance procedure)፣ በሚከተሉትን-ሁኔታዎች ውስጥ ለሚቀርቡት ሁሉም ቅሬታዎች ወይም አቤቱታዎች በስራ-ላይ የሚውሉም-ይሆናል:

(a) የግለሰቡ መብቶች፣ ተከልክለዋል ወይም ተቋርጠዋል የሚል-ክስ በሚኖርበት ጊዜ፤

(b) የማንኛውም ግለሰብ - በዘፈቀደ ወይም ተገቢ-ባልሆነ ድንጋጌ፣ ሂደት፣ ወይም የፀባይ መደበኛነት ውስጥ አላግባብ ተጠቂ ሲሆኑ፣

(c) አንድ-ግለሰብ፤ የማንጓጠጥ (bullying) ወይም ትንኮሳ - የወሲባዊ ትንኮሳ (Sexual harassment)ን ጨምሮ፣ ተጠቂ በሚሆንበት-ጊዜ፤ እና

(d) በዚህ 'title' ውስጥ የተለየ የቅሬታ ሂደት ወይም የፍርድ-ቤት ተሰሚነት ሂደት (hearing process) በሌለው በሕግ-የተሰጠውን መብት የሚጣስ ሌላ ማንኛውም ዓይነት-ነገር።

405.4 ይህን ክፍል/section ተከትሎ ቅሬታን ፋይል ለሚያደርግ ግለሰብ ወይም ቅሬታ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ-የሚሆን ግለሰብ ላይ-መሠረት ባደረገ ሁኔታ፣ ማንም ግለሰብ በአድልዎ-መገለል ወይም በሌላ-ሁኔታ የበቀል እርምጃ ሊወሰድበት አይገባም።

405.5 በ § B 405.1 ወይም § E 405.3 ክፍል/section ላይ-በተቀመጠው-መሠረት - በተፈጠረ-ጉዳይ ላይ ቅሬታን-የሚያቀርብ ግለሰብ፤ በዚህ ክፍል/section ውስጥ የተካተተውን ሂደት-መከተል አለበት። ቅሬታው፤ ሌላውን ግለሰብ ወክሎ - በጠበቃ ወይም ፈቃድ-በተሰጠው ወኪል አማካኝነት ፋይል-ሊደረግ ይችላል።

(a) ቅሬታውን የሚያቀርበው ግለሰብ (ቅሬታ-አቅራቢ/the grievant)፣ ለርዕሰ-መምህሩ ወይም ለሌላ ለፕሮግራሙ ወይም እንቅስቃሴው ኃላፊ-ለሆነ - የትምህርት ቤቱ ሹም፣ ኢ-መደበኛ የሆነ አቤቱታ ሊያቀርብ-ይችላል። ቅሬታ-አቅራቢው፤ ከርዕሰ-መምህር ወይም ለፕሮግራሙ ወይም እንቅስቃሴው ኃላፊ ለሆነ ሹም-ሣይሆን - ለአስተማሪ ወይም አስተዳደር አቤቱታውን የሚያቀርብ ከሆነ፤ ያ-ሰው - በቅሬታ-አቅራቢው ፈቃድን-በማግኘት፣ ስለ አቤቱታው ምንነት፣ ለርዕሰ-መምህር ወይም ለፕሮግራሙ ወይም እንቅስቃሴው ኃላፊ-ለሆነ ሹም ማሳወቅ-ያስፈልገዋል።

(b) ርዕሰ-መምህሩ - ለቅሬታ-አቅራቢው ተጠያቂ-ሆነው የቀረቡ-ከሆነ ወይም በቅሬታው ዙሪያ ባሉ ሁኔታዎች ውስጥ የተካፈሉ-ከሆኑ፤ ቅሬታ-አቅራቢው - በርዕሰመምህሩ ትምህርት ቤት ላይ ስልጣን ላለው የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ (Instructional Superintendent)፣ ኢ-መደበኛ ቅሬታ ማቅረብ አለበት።

(c) ኢ-መደበኛ ቅሬታን የተቀበለው ሰው፤ በኢ-መደበኛ በሆነ መንገድ ችግሩን መርምሮ ለመፍታት መሞከር ያለበት ሲሆን - እነዚህ ጨምሮ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ ሣይወሰን - በስብሰባዎች፣ ኮንፈረንሶች እና ውይይቶች አማካኝነት መፍታት-አለበት። ግለሰቡ፤ ጉዳዩን ለመመርመር የተወሰዱ እርምጃዎችን ሁሉ - በጽሁፍ የሰነድ ማስረጃ ማቅረብ አለበት።

(d) ኢ-መደበኛ ሂደት ላይ የውሳኔ ሃሳብ ወይም ውሳኔውን፣ በዳይሬክተሩ ወይም በሌላ የትምህርት ቤት ባለስልጣን፣ ለቅሬታ አቅራቢው - ኢ-መደበኛ ቅሬታውን ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በአስር (10) የትምህርት ቀናት ውስጥ - ውሳኔ-ይሰጣል።

ተገቢ-የሆነው የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ/Instructional Superintendent፤ ስለ ኢ-መደበኛ ቅሬታው እና ምርመራው ያሳውቃል እና ቅሬታውን ለመፍታት ርዕሰመምህሩ ወይም ሌላ የትምህርት ቤት ባለስልጣንን ማማከር ይችላሉ።

(e) በተሰጠው ውጤቱ ያልተደሰተ - ወይም ኢ-መደበኛ ሂደቱን ላለመጠቀም የመረጠ - ቅሬታ-አቅራቢ፤ በትምህርት ቤቱ ላይ አጠቅላይ ስልጣን ካለው ከትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ ስራ-አስኪያጁ/Instructional Superintendent ወይም ሌላ ኃላፊነት ላለው የትምህርት ቤት ባለስልጣን - የጽሁፍ ቅሬታን ለማቅረብ ይችላል። የጽሁፍ ቅሬታዎች፤ ክስተቱ ወይም የቅሬታ ሁኔታው ከደረሰ -- በአርባ አምስት (45) የቀን-መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ወይም ኢ-መደበኛ ሂደት በተጠናቀቀ በአስር (10) የቀን-መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ - ማንኛውም-ካለ፣ ከሁለቱ-በረዘመው ቀን፤ መቅረብ አለበት። የማስገቢያው የጊዜ-አቀማመጦች የሚተመኑት፣ ቅሬታ-አቅራቢው ትንኮሳውን ያልተገነዘበው ወይም የማያውቅ ሆኖ-በሚገኝበት ጊዜ-ነው።

(f) ሁሉም የአቤቱታ-ቅሬታዎች፣ የሚከተሉትን መረጃዎች - በቅሬታ-አቅራቢው ሊታወቅ እስከሚችለው ድረስ፣ ማካተት-አለበት:

(1) የቅሬታ-አቅራቢው ስም እና አድራሻ፤

(2) ቅሬታ-አቅራቢው፣ ከትምህርት ቤቱ ጋር ያለው ግንኙነት (ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ ወይም ሌላ)፤

(3) ክስተቱ-የተፈጸመበት ቀን፣ በግምት-ምን ሰዓት ላይ እንደሆነ፣ እና ቦታው፤

(4) በክስተቱ-ላይ የነበረውን፣ የማንጓጠጥ ወይም ትንኮሳ ዓይነት፤

(5) ትንኮሳ-ነው ተብሎ-የተወሰደውን ድርጊቶች የፈጸመውን ሰው(ዎች) የመለየት-ሂደት፤

(6) ተከስቷል-የተባለው ትንኮሳ ወደ ሌላ ሰው(ዎች) ላይ ያነጣጠረ ከሆነ፣ የእነዚህ ሰዎች ማንነት፤

(7) ማንኛውም ምስክሮች በቦታ-የነበሩ መሆንና-አለመሆኑን፣ እና የእነርሱን ማንነት፤ እና

(8) ማንኛውም የቃል-መግለጫዎች ወይም አካላዊ ግንኙነትን ጨምሮ፣ ስለ ክስተቱ የተለየ እውነታዊ-ሁኔታን መግለጫ።

(g) የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ/Instructional Superintendent ወይም ሌላ ኃላፊነት ያለው የትምህርት ቤት ባለስልጣን፤ ከቅሬታ አቅራቢ(ዎች)፣ ተማሪዎች፣ ወላጆች፣ አስተማሪዎች፣ ሌሎች የትምህርት ቤት ሹሞች እና ሌሎች ተሳታፊ-የሆኑ አካላት ጋር - ኮንፈረንስ በማካሄድ እና አስፈላጊ-ሆኖ ሲገኝ ከህግ አማካሪ፣ ከ‘Title IX’ አስተባባሪ ወይም ከSection 504 አስተባባሪ ጋር-ሆኖ በመመካከር፣ መደበኛ ምርመራን በመጀመር፣ በጽሁፍ-የቀረበውን ቅሬታ ለመፍታት ይሞክራሉ።

በተጨማሪም፤ ምርመራው - በአቤቱታ-አቅራቢው የቀረበውን ማንኛውንም መረጃ መመርመር እና ቅሬታ-አቅራቢው ለይቶ-ካቀረባቸው ምስክሮች ጋር ቃለ-መጠይቅ ማድረግን፣ ማካተት አለበት።

(h) የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ ስራ-አስኪያጁ/Instructional Superintendent፣ ለቅሬታ-አቅራቢው በትምህርት ቤቱ የቀረበውን ማስረጃ ወይም ሰነድ ያቀርባል፣ እና ለቅሬታ-አቅራቢው ይህን ማስረጃ ውድቅ ለማድረግ ዕድል ይሰጣል።

(i) የጽሁፍ ቅሬታውን የሚመረምሩት - የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ ስራ-አስኪያጁ/Instructional Superintendent ወይም ለሌላ ኃላፊነት ላለው የትምህርት ቤት ባለስልጣን፤ ለቅሬታ-አቅራቢው እና ለትምህርት ቤቱ ርዕሰ-መምህር - የጽሁፍ ምላሽ-ያቀርባሉ።

(j) የጽሁፍ ቅሬታው በደረሳቸው በአስር (10) የትምህርት ቀናት ውስጥ፣ የጽሁፍ ምላሽን ያቀርባሉ፤ ምርመራው ረዘም-ያለ ጊዜ የሚፈጅ-ከሆነ - ለቀረቡት-አካላት/parties - የዘገየበትን ምክንያት እና የሚገመተውን የጊዜ-አቀማመጥ ጨምሮ - እንዲያውቁት-ይደረጋል።

(k) በትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጁ/Instructional Superintendent ምላሽ - ቅሬታ-አቅራቢው ያልተደሰተበት-ከሆነ፣ በቻንስለሩ ለተመደበ ሌላ የትምህርት ቤት ሹም - አቤቱታ-አቅራቢው፣ አቤቱታውን ፋይል ሊያደርግ ይችላል። አቤቱታው፤ በተቀበሉ ወይም ከመጀመሪያ ምላሽ ማስታወቂያው በአስር (10) የቀን-መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ፣ ፋይል ይደረጋል።

(l) የተመደበው የትምህርት ቤት ሹም፤ የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጁ/Instructional Superintendentን ምርመራ እና ግኝቶች ላይ ምልከታ-በማድረግ፣ እና በቅሬታው ላይ ተጨማሪ ምርመራ በማካሄድ - ሁሉንም ተሳታፊ አካላት/parties ያካተተ ስብሰባ ማድረግን እና አስፈላጊ-ከሆነ ከህግ አማካሪ ጋር መመካከርን-ጨምሮ፣ ቅሬታውን ለመፍታት ይሞክራሉ።

(m) የተመደበው የትምህርት ቤት ሹም፤ የአቤቱታ-ይግባኙ በደረሰው በአስር (10) የትምህርት-ቀናት ውስጥ፣ ለቅሬታ-አቅራቢው እና ለትምህርት ቤቱ ርዕሰ-መምህር፣ የጽሁፍ ምላሽ መስጠት አለበት።

(n) ቅሬታ-አቅራቢው፤ በምላሹ ካልረካበት ወይም የተመደበው የትምህርት ቤት ሹም - በቁ-ውሳኔን ማግኘት ካልቻለ፤ ቅሬታ-አቅራቢው ወይም የተመደበው የትምህርት ቤት ሹም - በጽሑፍ ምላሽ በተሰጠው በአስር (10) የቀን-መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ፣ ቅሬታውን - ተገቢ እና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት፥ በቅሬታ-አቅራቢው የምልከታ-ማድረጊያ ፓኔል (review panel) ፊት እንዲቀርብ መጠየቅ ይችላል። ፓኔሉ (The panel)፤ በቻንስለር ወይም ተወካዩ የተሾሙ - ሦስት (3) ሰዎችን ያቀፈ ሲሆን፣ የSection 504 አስተባባሪ፣ የ'Title IX' አስተባባሪ፣ ከDCPS የተገዢነት-ቢሮ ውስጥ ያሉ ግለሰቦች፣ የጠቅላይ ምክር ቤት ቢሮ፣ ሌሎች የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጆች/Instructional Superintendents ወይም የትምህርት ቤት ሹሞች እና ሌሎች በቅሬታ-አቅራቢው ስለተነሱት ጉዳዮች ከስልጠና እና እውቀት ጋር የሚገኙ ፍላጎት-የሌላቸውን ሰዎችን - የሚያካትት-ይሆናል።

(o) በምልከታ-አድራጊው ፓኔል (review panel) ፊት የቀረቡት-ሁሉም ጉዳዮች ውስጥ፤ ፓኔሉ/panel - የጽሁፍ ግኝቶቹን ለተመደበው የትምህርት ቤት ሹም እና ትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ ስራ-አስኪያጅ/Instructional Superintendent እና በርዕሰ-መምህር የቀረበ የአስተያየት ሃሳቦችን - ማቅረብ-ያለበት ሲሆን፣ የጽሁፍ ግኝቶችን እና የቀረቡ-ሃሳቦች ቅጂ/copy - ለቅሬታ-አቅራቢውም መሰጠት-አለበት። ግኝቶቹ እና የቀረቡት-ሃሳቦች፤ በፓነሉ (the panel) - በዚህ ክፍል/Section §E405.5 (n) ላይ የተጠቀሰውን በተቀበሉበት በአስር (10) ቀናት ውስጥ፣ የሚሰጥ ይሆናል።

(p) ግኝቶቹ እና የውሳኔ-ሃሳቦቹ በደረሰበት - በአምስት (5) ቀናት ውስጥ፣ በተወከሉ የትምህርት ቤት ሹም/designated school official፣ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሰጣሉ፤ ይህም የትምህርት ቤቱ ስርዓት የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሆናል። የተወከሉት የትምህርት ቤት ሹም/The designated school official፤ ስለ ውሳኔው - ለቅሬታ-አቅራቢው፣ የትምህርት-አሰጣጥ ጠቅላይ ስራ-አስኪያጁ እና ርዕሰ-መምህሩ፣ እና አስፈላጊ-ከሆነ ደግሞ - ለቅሬታ-አቅራቢው ጠበቃ ወይም ስልጣን-ያለው ተወካይ - በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት።

(q) ቅሬታ-አቅራቢው፣ በተጨማሪም - አቤቱታውን በቀጥታ ከአሜሪካ የትምህርት መምሪያ፣ የሰው-ልጅ መብቶች ቢሮ (U.S. Department of Education, Office of Civil Rights) ጋር፤ በዚህ ክፍል/section ውስጥ ያሉትን ማንኛውም ሂደቶችን - ሳይጠቀም፣ ወይም ሳያጠናቅቅ - አቤቱታውን ፋይል ማድረግ ይችላል። ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት፣ በhttp://www.ed.gov/ocr/complaintprocess.html ላይ ተመልከቱ ወይም በ(202) 453---6020 ደውሉ።

(r) ቅሬታ-አሰሚው፣ አቤቱታውን በቀጥታ ከኮሎምብያ ዲስትሪክት ኮሚሽን - በሰብዓዊ መብቶች (District of Columbia Commission on Human Rights)፣ በዚህ ክፍል/section ውስጥ የተካተቱትን ሂደቶች ሳይጠቀም ወይም ሳይከተል፣ ፋይል ማድረግም ይችላል። በዚህ ክፍል/section ውስጥ፣ ከኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (District of Columbia Commission on Human Rights) ጋር፣ ቅሬታ-ለማቅረብ መብቶችን ወይም መስፈርቶችን የሚተካ-ነገር የለም።
ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት በhttp://www.ohr.dc.gov ላይ ተመልከቱ ወይም በ(202) 727---4559 ደውሉ።

## አባሪ/Appendix E---የ'Chapter 25' - ለእገዳዎች/Suspensions፣ የቅሬታ ሂደት:

B2505.14 ከአስራ-አንድ (11) ቀናት ያነሰ-ለሆነ ጊዜ፣ ታግዶ-የነበረ ተማሪ፣ እገዳው ላይ የይግባኝ-አቤቱታ እንደሚከተለው ማቅረብ-ይችላል:

(a) የአጭር-ጊዜ እገዳው/Short--Term Suspension፣ ለርዕሰ-መምህሩ የይግባኝ-አቤቱታው ሊቀርብ

(b) የመካከለኛ-ጊዜ እገዳ/Medium--Term Suspension፣ በቻንስለሩ ለተወከለው ሰው፣ የይግባኝ-አቤቱታው ሊቀርብ-ይችላል።

(c) ሁሉም የአቤቱታ-ይግባኞች - በተማሪው ወላጅ ወይም አሳዳጊ ወይም አዋቂ-በሆነው ተማሪ፣ ወይ - በቃል ወይም-ደግሞ በጽሁፍ ለርዕሰ-መምህሩ ወይም በቻንስለር ለተመደበው ሰው፣ እንደየአግባቡ፣ የእገዳ ማስታወቂያን ከተቀበሉ በኋላ፣ ከሁለት (2) የትምህርት-ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ፣ እና የእገዳው መደበኛ የጽሁፍ ማስታወቂያ ከመድረሱ በፊት - ሊደረግ ይችላል። በቃል-የተደረጉ የይግባኝ-አቤቱታ (appeal)፣ ጥያቄውን በሚቀበለው-ሰው፣ በጽሁፍ መቀመጥ አለበት።

(d) ሁሉም የአቤቱታ-ይግባኞች - በርዕሰ-መምህሩ (ለአጭር-ጊዜ እገዳዎች) ለሆኑት ወይም በቻንስለር በተመደበው ሰው (ለመካከለኛ-ጊዜ እገዳዎች) - ከአንድ (1) የትምህርት ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ፣ ተሰሚነት-የሚያገኙ ይሆናል። በአዋቂ-የሆነው ተማሪ ወይም ለአካለ-መጠን ያልደረሰ ተማሪ ወላጅ ወይም አሳዳጊ - ጥያቄውን-በሚያቀርቡ ጊዜ፤ የይግባኙ ጊዜ እስከ ሶስት (3) የትምህርት-ቀናት ሊራዘም ይችላል። አቤቱታው፤ አስፈላጊ-ሆኖ ከተገኘ - በጤና፣ በስራ፣ ወይም በልጅ-እንክብካቤ/childcare ምክንያት - በወላጅ ወይም አሳዳጊ ከተጠየቀ - በስልክ ሊከናወን ይችላል።

(e) ተማሪው ወይም የእርሱ ወይም የእርሷ ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣ ማስረጃን ማምጣት እና ምስክሮች እንዲናገሩ መጠየቅ ይችላሉ።

(f) በኮንፈራንሱ ማጠቃለያ ላይ፣ ርዕሰ-መምህሩ ወይም በቻንስለር የተመደበው-ሰው፣ እንደየአግባብነቱ - የመጨረሻ ውሳኔውን ይሰጣሉ።

(g) ከኮንፈራንሱ በኋላ፣ ከአንድ (1) የትምህርት-ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ፣ ርዕሰ-መምህሩ ወይም በቻንስለር የተመደበው-ሰው፣ እንደየአግባብነቱ፣ ለተማሪው እና ለእርሱ ወይም ለእርሷ ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣ በቻንስለር ለተመደበው-ሰው፣ እና ለታዳጊ-ወጣት ተሳትፎ ቢሮ/Office of Youth Engagement ዋና-ኃላፊው - የኮንፈረንሱን ሂደት የጽሁፍ ማጠቃለያን - የመጨረሻውን ውሳኔ ጨምሮ፣ መስጠት አለባቸው።

B2505.15 ለአስራ-አንድ (11) ቀናት ወይም ከዚያ-በላይ ለሆነ ጊዜ ወይም ወዲያው-ክስተቱን ተከትሎ - የትምህርት ዓመቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ - አድርጓ-የተባለውን ጥሰት በተመለከተ፣ ታግዶ-የቆየ ተማሪ።

B2507.7 የረጅም-ጊዜ እገዳ/Long---Term Suspension፤ በቀጥታ ከታዳጊ-ወጣት ተሳትፎ ቢሮ/Office of Youth Engagement ዋና-ኃላፊው ጋር - አቤቱታው ሊቀርብ-ይችላል።
(a) ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣ ወይም አዋቂ-የሆነ ተማሪ - የረጅም ጊዜ መታገድ/Long---Term Suspensionን - ወደ ታዳጊ-ወጣት ተሳትፎ ቢሮ/Office of Youth Engagement ዋና-ኃላፊው የይግባኝ-ጥያቄው ለማስገባት የሚፈልጉ፤ የረጅም ጊዜ እገዳ/Long---Term Suspension ማስታወቂያው በደረሳቸው - በአምስት (5) የትምህርት-ቀናት ውስጥ፣ ሃሳብ-የቀረበለትን የረጅም ጊዜ እገዳ/Long---Term Suspension ይግባኝ-ለማለት፣ በጽሁፍ ወይም በቃል ጥያቄ ማቅረብ አለባቸው። ጥያቄው - በቃል-የቀረበ ከሆነ፣ ጥያቄውን በሚቀበለው-ሰው፣ በጽሁፍ ተመዝግቦ-መቀመጥ አለበት።
(b) የይግባኝ-ጥያቄውን በሚቀበሉበት-ጊዜ፣ የታዳጊ-ወጣት ተሳትፎ ቢሮ/Office of Youth Engagement ዋና-ኃላፊው፤ ከወላጅ ወይም አሳዳጊ፣ ወይም አዋቂ-ከሆነው ተማሪ ጋር፣ የይግባኝ ጥያቄው በደረሰው በሦስት (3) የትምህርት ቀናት ውስጥ፣ ኮንፈረንስ እንዲካሄድ ቀጠሮ ይይዛሉ።
(c) በኮንፈረንሱ ወቅት-ላይ፤ ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣ ወይም አዋቂ-የሆነው ተማሪ፤ አቤቱታውን ወይም አቤቱታዋን የሚደግፍ ክርክሮችን ሊያቀርቡ-ይችላሉ። ተማሪው፤ ወኪል ወይም ሕጋዊ ካውንስል - በወላጅ ወይም በአሳዳጊ ወይም በአዋቂ-ተማሪው የተመረጠ - ሊኖረው የሚያችል መብት አለው፤ ነገር ግን በግድ-መደረግ ያለበት ነገር አይደለም። አቤቱታው፤ በወላጅ ወይም አሳዳጊ ከተጠየቀ - በስልክ ሊከናወን ይችላል። ኮንፈረንሱ፤ በማንኛውም አካላቶች/parties - ሊቀዳ-የሚችል ይሆናል።
(d) ኮንፈረንሱ ከተጠናቀቀበት - ከሁለት ያልበለጠ (B2) የትምህርት-ቀናቶች በኋላ፣ የታዳጊ-ወጣት ተሳትፎ ቢሮ/Office of Youth Engagement ዋና-ኃላፊው - የመጨረሻውን ውሳኔ ያቀርባሉ። የታዳጊ-ወጣት ተሳትፎ ቢሮ/Office of Youth Engagement ዋና-ኃላፊው፣ ለወላጅ ወይም አሳዳጊ፣ ወይም አዋቂ-ለሆነው ተማሪ እና በቻንስለር ለተመደበው ሰው፤ የኮንፈረንስ ሂደቶችን እና ውሳኔን - በጽሁፍ ማጠቃለያ ይሰጣል።

B2507.8 የታዳጊ-ወጣት ተሳትፎ ቢሮ/Office of Youth Engagement ዋና-ኃላፊው፣ ከመሣሪያ-ነጻ ትምህርት ቤቶች ድንጋጌ (Gun---Free Schools Act) በመጣስ - መባረርን-የፈቀደ ከሆነ፤፣ ወላጅ ወይም አሳዳጊ ወይም አዋቂ-የሆነው ተማሪ - በ§ B2507.9 በተገለጸው ሂደት መሠረት፣ ውሳኔውን ለቻንስለር ይግባኝ-ማለት ይችላሉ። የቻንስለሩ ውሳኔ - የመጨረሻ የሚሆን እና ለወላጅ ወይም አሳዳጊ፣ ወይም አዋቂ-ለሆነው ተማሪ፣ በቻንስለር ለተመደበው-ሰው እና ተማሪው በተባረረበት ትምህርት ቤት-ውስጥ ርዕሰ-መምህር ለሆኑት፤ በጽሁፍ መቅረብ አለበት።

B2507.8 በዚህ ክፍል ውስጥ የተካተቱት ሌሎች ድንጋጌዎች ቢኖሩም-እንኳን፣ በቻንስለሩ የተመደበው-ሰው፣ በራሱ ወይም በራሷ ውሳኔ፣ ያለ ርዕሰ-መምህሩ ወይም ተወካዩ የምክር-ሃሳብ - የመባረር እርምጃውን ሊጀምር ይችላል።

B2507.9 መባረር (Expulsion)፤ በቀጥታ ወደ ቻንስለሩ ይግባኝ ሊባል ይቻላል።
(a) መባረር (Expulsion)ን በቀጥታ-ወደ ቻንስለሩ ይግባኝ-ለማለት የሚፈልግ - ወላጅ ወይም አሳዳጊ ወይም አዋቂ-የሆነ ተማሪ፣ የመባረሩ ማስታወቂያ በደረሰው በአምስት (5) የትምህርት-ቀናት ውስጥ፣ የቀረበውን-ሃሳብ - በጽሁፍ ወይም የቃል ጥያቄውን-በማቅረብ፣ የይግባኝ-ጥያቄውን ማስገባት-አለባቸው። ጥያቄው - በቃል-የቀረበ ከሆነ፣ ጥያቄውን በሚቀበለው-ሰው፣ በጽሁፍ ተመዝግቦ-መቀመጥ አለበት።

(b) የይግባኝ-ጥያቄውን ከተቀበለ በኋላ፣ ቻንስለር ወይም ወኪሉ፤ ከወላጅ ወይም አሳዳጊ፣ ወይም አዋቂ-ከሆነው ተማሪ ጋር፣ የይግባኝ ጥያቄው በደረሰው በሦስት (3) የትምህርት ቀናት ውስጥ፣ ኮንፈረንስ እንዲካሄድ ቀጠሮ ይይዛሉ።
(c) በኮንፈረንሱ ወቅት-ላይ፤ ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣ ወይም አዋቂ-የሆነው ተማሪ፤ አቤቱታውን ወይም አቤቱታዋን የሚደግፍ ክርክሮችን ሊያቀርቡ-ይችላሉ። ተማሪው፤ ወኪል ወይም ሕጋዊ ካውንስል - በወላጅ ወይም በአሳዳጊ ወይም በአዋቂ-ተማሪው የተመረጠ - ሊኖረው የሚያችል መብት አለው፤ ነገር ግን በግድ-መደረግ ያለበት ነገር አይደለም። አቤቱታው፤ በወላጅ ወይም አሳዳጊ ከተጠየቀ - በስልክ ሊከናወን ይችላል። ኮንፈረንሱ፤ በማንኛውም አካላቶች/parties - ሊቀዳ-የሚችል ይሆናል።
(d) ኮንፈረንሱ ከተጠናቀቀበት - ከሁለት ያልበለጠ (B2) የትምህርት-ቀናቶች በኋላ፣ ቻንስለሩ - የመጨረሻውን ውሳኔ ያቀርባሉ። ቻንስለሩ፤ ለወላጅ ወይም ለአሳዳጊ ወይም አዋቂ-ለሆነው ተማሪ፣ በቻንስለር የተሾመ-ሰው እና የታዳጊ-ወጣት ተሳትፎ ቢሮ/Office of Youth Engagement ዋና-ኃላፊ - የኮንፈረንስ ሂደቶችን እና የእርሱን ወይም የእርሷን የመጨረሻ ውሳኔ፣ በማጠቃለያ ጽሁፍ ያቀርባሉ።

**B2508 በቻንስለር (CHANCELLOR)**

B2508.1 በማንኛውም እንዲደረግ-በቀረበ የዲስፕሊናዊ እርምጃ ላይ፣ ቻንስለሩ - ዳግም-ምልከታ ወይም ማስተካከያ ሊያደርጉ-ይችላሉ። የዲሲፕሊን እርምጃው ዋስትና-እንደሌለው - ቻንስለሩ ከወሰኑ፣ ውሳኔው - ድርጊቱ ከተመሠረተበት ክስተት ጋር በተገናኘ፣ የዲሲፕሊን እርምጃ ሪፖርቶችን ጨምሮ - የዲሲፕሊን እርምጃው ሁሉንም የትምህርት ቤት መዛግብት እንዲወገዱ የሚያዝ መግለጫን የሚያካትት-ሲሆን፣ እስከአሁን በእነዚያ ሪፖርቶች ውስጥ በየግል ተማሪውን የሚለየው ሆነው በቀረቡት እውነታዎች ላይ፣ ማንኛውም የDCPS ህግ ወይም ፖሊሲ መጣስ እንደሌለበት ተወስኗል።

B2508.2 ሁሉንም የዲሲፕሊን እርምጃዎች በተመለከተ፤ መባረር/Expulsionን ጨምሮ - ቻንስለሩ፣ ማንኛውንም የቀረበውን የዲሲፕሊን እርምጃ መሻር ወይም ማሻሻል ይችላሉ። ቻንስለሩ፤ ለማንኛውም የዲሲፕሊን እርምጃ - የማሻሻያ የጽሁፍ ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት።